# የግብረገብ ትምህርት

# የመምህራን መምሪያ

# 5ኛ ክፍል

**ተርጓሚዎች**

ፍራንኦል ዋቅጅራ

ታምራት ለገሠ

ተስፋዬ አመኑ

**አርታኢዎች**

ግሩም ጥበቡ

ታምሩ ገለታ

**ገምጋሚ**

ደረጀ መኮንን

**ግራፍክስ**

ታደሰ ድንቁ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2015/2023

ይህ የመምህራን መምሪያ በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ በ2015/2023 ተስማምቶ ወደ አማርኛ የተተረጎመ ነው። የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው። ይህን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፍቃድ በየትኛውም መልኩ ማሳተምም ሆነ ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው፡፡

## ምስጋና

ይህ የመምህራን መምሪያ በትምህርት ሚኒስቴር አመራርት በሀዋሳ ፣ጅማ፣ አዲስ አበባና ባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው፡፡ በመቀጠል በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ቅንጅት ተተርጉሞና ተስማምቶ ተዘጋጀ፡፡

በመሆኑም በዚህ ስራ ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው የትምህርት ሚኒስቴር፣ የዩኒቨርስቲ አዘጋጆችና በክልላችን ላሉ የትምህርት ባለሙያ ተርጓሚዎችና አስማሚዎች በሙሉ የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ላቅ ያለ ምስጋና አለው፡፡

# ማውጫ

ምዕራፍ አንድ   ኃላፊነት ....................................................................1
1.1. ትምህርት አንድ፡ የኃላፊነት ምንነት ........................................2
1.2. ትምህርት ሁለት፡ ኃላፊነትን መወጣት ......................................5
1.3. ትምህርት ሶስት፡ የኃላፊነት አስፈላጊነት ..................................7
1.4 ትምህርት አራት፤ የተጠያቂነት ደረጃዎች ................................10
1.5. ትምህርት አምስት፤ የግብረገባዊ ኃላፊነት አይነቶች ................13
ምዕራፍ ሁለት 18ጠንክሮ የመስራት ባህል ..........................................18
2.1.ትምህርት አንድ፡ የጠንክሮ መስራት ባህል ምንነት ...................19
2.2. ትምህርት ሁለት፡ የጠንክሮ መስራት ባህል አስፈላጊነት...........21
2.3. ትምህርት ሶስት፡ የጠንካራ ተማሪ የስራ ባህል መገላጫዎች.....24
2.4. ትምህርት አራት፡ የንባብ ባህል................................................27
2.5 ትምህርት አምስት፡ የንባብ ባህልን የማስፋፋት ስልቶች ...........29
ምዕራፍ ሦስት_የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታ..................................................33
3.1. ትምህርት አንድ፡ የትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ጽንሰ ሀሳብ ..........34
3.2. ትምህርት 2፡ የትክክለኛ ውሳኔ ችሎታዎች ባህሪያት ...............37
3.3. ትምህርት 3፡ ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ደረጃዎች..................39
3.4. ትምህርት 4፡ ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነት ..............42
3.5. ትምህርት 5፡ የትክክለኛ ውሳኔ እንቅፋቶች .............................45
3.6. የምዕራፍ 3 የክለሳ ጥያቄ መልስ..............................................48
ምዕራፍ 4_የአካባቢ እንክብካቤ..........................................................49
4.1. ትምህርት 1፡ የአካባቢ ምንነት..................................................50
4.2. ትምህርት 2፡ የአካባቢ እንክብካቤ ምንነት...............................52
4.3. ትምህርት 3፡ የአካባቢ እንክብካቤ አስፈላጊነት ........................55
4.4. ትምህርት 4፡ አካባቢን የመንከባከብ መንገዶች........................58

4.5. ትምህርት 5፡ ለአካባቢ እንክብካቤ አለመስጠት የሚያስከትለው ጉዳት ........ 61
4.6. የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ........ 63
ምዕራፍ 5 የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር ........ 64
5.1. ትምህርት 1፡ የማህበራዊ ሚዲያ ምንነት ........ 65
5.2. ትምህርት 2፡ የማህበራዊ ሚዲያ ጠቀሜታ ........ 68
5.3. ትምህርት 3፡ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር ........ 71
5.4. ትምህርት 4፡ ማህበራዊ ሚዲያን አላግባብ የመጠቀም ጉዳቶች 74
ምዕራፍ 6_የባህል ግንኙነት ........ 78
6.1. ትምህርት 1፡ የባህል ግንኙነቶች ምንነት ........ 79
6.2. ትምህርት 2፡ የባህል ግንኙነት አስፈላጊነት ........ 81
6.3. ትምህርት 3፡ በባህልና በሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) መካከል ያለ ግንኙነት ........ 84
6.4. ትምህርት 4፡ የባህል ግንኙነቶች መገለጫዎች ........ 86
የ5ኛ ክፍል ግብረገብ ትምህርት መርሃ ትምህርት ........ 90

# ምዕራፍ አንድ

# ኃላፊነት

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ኃላፊነትን እና የኃላፊነት አስፈላጊነቱን ያብራራል። በተጨማሪም የኃላፊነት ምንነት፣ የኃላፊነት ዓይነቶችን እና የሞራል ኃላፊነትን ያስተምራል። እነዚህን ይዘቶች ለማስተማር የቡድን ውይይት፣ ማብራሪያ፣ ሠርቶ ማሳያ፣ ትረካ፣ ጉብኝት፣ ጥያቄ እና መልስ፣ ዘገባ፣ ጽብረቃ እና የመሳሰሉት የማስተማር ዘዴዎች ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል።

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች**

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- የኃላፊነት ምንነትን ይገልጻሉ፤
- ኃላፊነት የመወጣት አስፈላጊነትን ይገነዛባሉ፤
- የኃላፊነት ደረጃዎችን ይለያሉ፤
- የህብረተሰቡን ስነ ምግባር እና እሴቶች ያደንቃሉ፤ ያከብራሉ፤
- ከአንድ ሰው የሚጠበቀውን ስነምግባርና እሴት ይዘረዝራሉ።

**ለምዕራፉ የተመደቡ ጠቅላላ ክፍለ ጊዜያት፡-** 19

**የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ይዘቶች**

ትምህርት 1፡ የኃላፊነት ምንነት

ትምህርት 2፡ ኃላፊነትን መወጣት

ትምህርት 3: ኃላፊነትን የመወጣት አስፈላጊነት

ትምህርት 4፡ የኃላፊነት ደረጃዎች

ትምህርት 5፡ የግብረገባዊ ኃላፊነት አይነቶች

## 1.1. ትምህርት አንድ፡ የኃላፊነት ምንነት

ለርዕሱ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ፡ 3

### 1.1.1. ይዘት

የኃላፊነት ምንነት

### 1.1.2. አጠቃላይ መግለጫ

ኃላፊነት ማለት ምን ማለት ነው? ስለ ኃላፊነት ስናወሳ ልንገነዘባቸው የሚገቡ ሁኔታዎች አሉ። እነሱም:

- ኃላፊነት፤
- ኃላፊነት መውሰድ፤
- በኃላፊነት ስሜት መስራት፤
- ተጠያቂ መሆን

በሌላ አገላለጽ፣ ኃላፊነት እኛ እንድንሠራ የሚጠበቅብንን ሥራ መሥራትና ውጤቱን መቀበል ነው (የሚያስመሰግንም ሆነ የሚያስወቅስን)።

ኃላፊነት ከአንድ ሰው የሚጠበቅን ስራ መስራት እና የስራን ውጤት መቀበል ነው። ኃላፊነት ተማሪዎች እንዲሰሩ የሚጠበቅባቸው ስራ ነው። ኃላፊነት መውሰድ ደግሞ ለተግባራቸው አድናቆት ወይም ትችት መቀበል ነው።

### 1.1.3. የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ወፍራም ወረቀት፣ ፎቶግራፎች፣ ካሴቶች፣ ፊልሞች፣ ስዕሎች፣ ግራፊክስ፣ ካርታዎች እና የመሳሰሉት

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

ተማሪዎች በቤተሰቦቻቸው፣ በጓደኞቻቸው እና በማህበረሰባቸው ውስጥ ምን አይነት ኃላፊነት እንዳለባቸው ይጠይቁ።

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

መምህሩ ስለ ኃላፊነት ለማስተማር የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች አስቀድመው ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

## የትምህርት አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን ያስተዋውቁ። ለምሳሌ፣ ኃላፊነት ምን እንደሆነ ታውቃለህ/ቂያለሽ?

ለቤተሰብህ/ሽ፣ ለትምህርት ቤትህ/ሽ እና ለማህበረሰብህ/ሽ ኃላፊነት እንዳለህ አስበህ/ሽ ታውቃለህ/ቂያለሽ?

### ለ. የዝግጅት አቀራረብ

- የሃላፊነቱን ምንነት ይግለጹ፤
- በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የተማሪዎችን ሃላፊነቶች ያብራሩ፣
- የኃላፊነት ባህሪን ይግለጹ፤
- ከተማሪዎች የሚጠበቀውን ባህሪ እና አተገባበሩን ይለዩ፤ እንዲሁም ያብራሩ።

### ሐ. ማጠናከሪያ

መምህር፤ ተማሪዎች የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች እንዲያብራሩ እና ተማሪዎች ያልጠቀሱትን ጠቃሚ ነጥቦች ይግለጹ።

## 1.1.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

ተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ምዘና ማካሄድ ይችላሉ።

- ኃላፊነት ምንድን ነው?
- በቤተሰብዎ ውስጥ ያለዎትን ኃላፊነት ትወጣለህ/ጫለሽ?
- ተጠያቂነት ምንድን ነው?
- የሚጠበቅብህን ሁሉ ታደርጋለህ/ጊያለሽ?
- በሚጠበቀው መንገድ እየሰራህ/ሽ ነው?

### ለ. ክትትል

- ተማሪዎች በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ ስላላቸው ኃላፊነት እንዲወያዩ እና እንዲያብራሩ አበረታቷቸው።
- የቡድን ውይይታቸውን እንዲያቀርቡ እርዷቸው።

### 1.1.5. የትምህርት አንድ ተግባራት መልሶች

**ተግባር 1**

1. አዎ፣ ባዳሳ በቤተሰቡ ውስጥ የተለያዩ ሃላፊነቶች አሉት።
2. በቤተሰባቸው ውስጥ ሊወጡ ከሚገባቸው ሃላፊነቶች መካከል ከጨዋታ በኋላ፣ ከምግብ በፊት እና በኋላ እጃቸውን መታጠብ፣ ጫማቸውን ማጠብ፣ ልብሳቸውን ማጠብ፣ ቤተሰባቸውን፣ ሽማግሌዎችንና ጎረቤቶቻቸውን ማክበር፣ ስህተታቸውን አምነው ይቅርታ መጠየቅ እና የመሳሰሉት ናቸው።

**ተግባር 2**

1. በተማሪዎች መልስ ላይ ተመስርተው መልሳቸው ‘አዎ’ ከሆነ ከተዘረዘሩት ኃላፊነቶች ውጪ እንዲዘረዝሩ አበረታቷቸው።
2. መዋሸት፣ መስረቅ፣ ሌሎችን መስደብ፣ ቤተሰብን አለማክበር፣ መጣላት እና የመሳሰሉት በምግባርና በህግ የተከለከሉ ናቸው።
3. በጎ ፈቃደኝነት ለተቸገሩ ሰዎች የምንሠራው የማይከፈልለት ሥራ ነው። ለምሳሌ፡ ለአረጋውን የፈረሰ ቤታቸውን መልሶ መስራት እና የመሳሰሉት ናቸው።

## 1.2. ትምህርት ሁለት፡ ኃላፊነትን መወጣት

**የተመደበ ክፍለ ጊዜ፡- 3**

### 1.2.1. ይዘት

- **ኃላፊነትን መወጣት**

### 1.2.2. አጠቃላይ መግለጫ

ኃላፊነትን መወጣት ተማሪዎች እንዲሠሩ የሚጠበቅባቸውን ማድረግ ነው። ተማሪዎች ሃላፊነታቸውን ካልተወጡ ስኬታማ ላይሆኑ ይችላሉ።

### 1.2.3. የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ወፍራም ወረቀት፣ ፎቶግራፎች፣ ካሴቶች፣ ፊልሞች፣ ሥዕሎች፣ ግራፎች፣ ካርታዎች፣ ወዘተ።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

ኃላፊነት የመወጣትን አስፈላጊነት ተማሪዎችን ጠይቋቸው። ተማሪዎችን በአነስተኛ ቡድኖች ይከፋፍሏቸው እና ኃላፊነት መወጣት በሚለው ላይ እንዲወያዩ አድርጉ።

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

መምህር፤ ተማሪዎችዎን ስለኃላፊነት ለማስተማር በቂ ዝግጅት ማድረግ አለብዎ።

**የትምህርት አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

ያለፉትን የትምህርት ይዘቶች አስታውሱ፤ የእለቱን ትምህርት ለማስተዋወቅ ጥያቄዎችን ይጠይቁ። ለምሳሌ;

- ኃላፊነት መውሰድ ጠቃሚ ነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ቢያለሽ?
- በስሜታችን እና በድርጊታችን ውስጥ ኃላፊነት ለምን እንደሚያስፈልግ ግለጽ/ጪ፡፡

**ለ. የዝግጅት አቀራረብ**

የኃላፊነት ባህሪያትን ይግለጹ፡፡

ኃላፊነት መውሰድ ተግባራችንን እና ስሜታችንን የመቆጣጠር ጥቅም እንዳለው ያስረዱ።

**ሐ. ማጠናከሪያ**

መምህር፤ ተማሪዎች ዋና ዋና ነጥቦቹን እንዲያብራሩ እና ጠቃሚ ነጥቦቹን እንዲደግሙ ይጠይቁ።

### 1.2.4. ምዘና እና ክትትል

**ሀ. ምዘና**

ተማሪዎችን የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቁ። ለምሳሌ፣ ሃላፊነታቸውን እንዴት እንደሚወጡ ይጠይቁ፡፡

**ለ. ክትትል**

ተማሪዎች በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት እና በማህበረሰቡ ውስጥ ስላላቸው ኃላፊነት እንዲወያዩ እና እንዲያብራሩ ያበረታቷቸው፤ የቡድን ውይይታቸውን እንዲያቀርቡ እርዷቸው።

### 1.2.5. የትምህርት ሁለት ተግባራት መልስ

**ተግባር 3**

ሀ. እንዲሰሩ የሚጠበቅባቸው ስራ

- ከምግብ በፊት እና ከጨዋታ በኋላ እጅን መታጠብ፣
- የቤት ውስጥ ሥራዎችን መሥራት፣
- ጫማቸውን ያፅዱ፣
- ልብሳቸውን ማጠብ፣
- ስህተታቸውን አምነው ይቅርታ ይጠይቁ፣
- የክፍል ንፅህናን መጠበቅ፣
- ትክክለኛ መቀመጫ እና የመሳሰሉት፡፡

ለ. እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው

- በጊዜ ቤት መገኘት፣
- ራስን ወይም ሌሎችን አለመጉዳት፣

- በአክብሮት መናገር፣
- ማህበራዊ ሚዲያዎችን በአግባቡ መጠቀም እና የመሳሰሉት፡፡

## 1.3. ትምህርት ሶስት፡ የኃላፊነት አስፈላጊነት

**የክፍለ ጊዜ መጠን፡ 3**

### 1.3.1 ይዘቶች

- ለድርጊታችን ኃላፊነት የመውሰድ አስፈላጊነት፤
- ስሜታችንን ለመቆጣጠር ኃላፊነት የመውሰድ አስፈላጊነት፤

### 1.3.2 አጠቃላይ መግለጫ

ኃላፊነትን መወጣት ተማሪዎች እንዲሠሩ የሚጠበቅባቸውን ማድረግ ነው፡ ተማሪዎች ሃላፊነታቸውን ካልተወጡ ስኬታማ ላይሆኑ ይችላሉ።

### 1.3.3 የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ወፍራም ወረቀት፣ ፎቶግራፎች፣ ካሴቶች፣ ፊልሞች፣ ሥዕሎች፣ ግራፎች፣ ካርታዎች፣ ወዘተ.

የማስተማር የመማር ዘዴዎች

ኃላፊነት የመውሰድን አስፈላጊነት ተማሪዎችን ይጠይቋቸው፤ ተማሪዎችን በአነስተኛ ቡድኖች ይከፋፍሏቸው እና የሚና ጫወታ እንዲጫወቱ ያድርጉ፤ እንዲሁም ስለ እግር ኳስ ጨዋታ እና ስለፈረስ ውድድር ለክፍል ተማሪዎች እንዲያብራሩ ያግዟቸው፤ ከመማሪያ መጽሃፉ ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎችም ይመልሱ።

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

መምህር፤ ተማሪዎችዎን ስለኃላፊነት ለማስተማር በቂ ዝግጅት ማድረግ አለብዎ።

**የትምህርት አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

ያለፉትን የትምህርት ይዘቶች አስታውሱ፤ የእለቱን ትምህርት ለማስተዋወቅ ጥያቄዎችን ይጠይቁ። ለምሳሌ፤

- ኃላፊነት መውሰድ ጠቃሚ ነው ብለህ/ሽ ታስባለህ/ቢያለሽ?
- የተጠያቂነት አስፈላጊነት ምንድነው?
- ከቤተሰብህ/ሽ እና ከትምህርት ቤትህ/ሽ ጋር ያለህ/ሽን ኃላፊነት ትወጣለህ/ጫለሽ?
- በስሜታችን እና በድርጊታችን ውስጥ ኃላፊነት ለምን እንደሚያስፈልግ ግለጽ/ጪ?

**ለ. የትምህርት አቀራረብ**

ኃላፊነት የመውሰድን አስፈላጊነት ያብራሩ።

ለድርጊታችን ኃላፊነት የመውሰድ እና ስሜታችንን የመቆጣጠርን አስፈላጊነት ያብራሩ።

**ሐ. ማጠናከሪያ**

መምህር ተማሪዎችዎን ዋና ዋና ነጥቦችን እንዲያብራሩ እና ጠቃሚ ነጥቦችን እንዲደግሙ ይጠይቋቸው።

### 1.3.4. ምዘና እና ክትትል

**ሀ. ምዘና**

ተማሪዎችን የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቁ። ለምሳሌ;

- ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚጫወቱበትን እና የሚሰሩበትን መንገድ፤
- ለአካላዊ ደህንነታቸው የሚደረግላቸውንና የሚያደርጉትን ጥበቃ፤
- ስራቸውን የሚሰሩበት መንገድ፤
- የግል ንብረት ጥበቃ፤
- ስህተት ሲሰሩ ስራቸውን ማመን መካዳቸውን፤ በእምነት ክህደት መልሳቸው ምን እንደተሰማቸው፤
- እንደዚህ አይነት ድርጊት ያላጋጠማቸው ከሆነ ቢያጋጥማቸው ምን እንደሚሰማቸው እና የመሳሰሉትን መጠየቅ፡፡

**ለ. ክትትል**

በቤተሰቦቻቸው፣ በትምህርት ቤቶች እና በማህበረሰባቸው ውስጥ ኃላፊነት የመውሰድን አስፈላጊነት እንዲወያዩ እና እንዲያብራሩ አበረታታቸው።

የቡድን ውይይታቸውን እንዲያቀርቡ እርዷቸው።

## 1.3.5. የትምህርት ሶስት ተግባራት መልሶች

**ተግባር 4**

1. ፈይሳ የጎረቤቱን መስኮት ሰብሮ በፍርሃት ሸሸ።

   የፈይሳ ኃላፊነት ስህተቱን መንገር እና አቶ ገመዳን ይቅርታ መጠየቅ ነበረበት።

2. ለቱራ ጥሩ ስራ ሰርቷል፣ አቶ ገመዳን ይቅርታ ጠይቆ ሃፊነቱን ተወጣ።

3. ለቱራን ብንሆን ኖሮ ይቅርታ እንጠይቅ ነበር።

## 1.4 ትምህርት አራት፤ የተጠያቂነት ደረጃዎች

### የተመደበ ክፍለ ጊዜ፡- 5

### 1.4.1 ይዘቶች

- የግለሰብ ተጠያቂነት
- የቤተሰብ እና ማህበራዊ ኃላፊነት
- የሀገር ኃላፊነት.

### 1.4.2 አጠቃላይ መግለጫ

ተጠያቂነትን መወጣት ማለት፤ በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ ከሌሎች ጋር መስራት እና የስራውን ስህተት ለማስተካከል ኃላፊነት መውሰድን ያካትታል። በቤተሰብ ውስጥ ያሉ የተማሪ ሃላፊነቶች ለምሳሌ ቤተሰባቸውን መርዳት፣ የቤት ንፅህናን መጠበቅ፣ ንፅህናቸውን መጠበቅ፣ የቤት ስራቸውን መስራት፣ ቤተሰብ ያዘዘውን መፈጸም እና የመሳሰሉት ናቸው።

በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ የተማሪ ሃላፊነቶች፣ ለምሳሌ የመማሪያ ክፍሎችን እና መቀመጫዎችን በሥርዓት እና በንጽህና መጠበቅ፣ መምህሩ የነገራቸውን ከእኩዮቻቸው ጋር ማድረግ እና የመሳሰሉት ናቸው።

### 1.4.3 የመማር ማስተማር ሂደት

#### የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ወፍራም ወረቀት፣ ፎቶግራፎች፣ ካሴቶች፣ ፊልሞች፣ ሥዕሎች፣ ግራፎች፣ ካርታዎች እና የመሳሰሉት

የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ስለ ሀላፊነት አይነት ተማሪዎችን ይጠይቋቸው፤ ተማሪዎችን በአነስተኛ ቡድኖች በመከፋፈል በራሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በማህበረሰቡ እና በሃገር መካከል ስላላቸው ሃላፊነቶች እንዲወያዩ እና በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያድርጉ።

ቅድመ ትምህርት ዝግጅት

መምህር፤ ተማሪዎችዎን ስለ ኃላፊነት ዓይነቶች ለማስተማር በቂ ዝግጅት ማድረግ አለብዎ።

**የትምህርት አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

በቀደመው ትምህርት የተማሩትን ኃላፊነትን የመውሰድን አስፈላጊነት ተማሪዎችን ይጠይቁ።

ስለ ሃላፊነተ ዓይነቶች የሚያውቁትን እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው።

**ለ. የትምህርት አቀራረብ**

የተማሪዎችን የግል ሀላፊነቶች ያብራሩ።

ለቤተሰቦቻቸው እና ለማህበረሰባቸው የተማሪዎችን ሀላፊነት ያብራሩ።

ተማሪዎች ለአገራቸው ያላቸውን ኃላፊነት ያብራሩ።

**ሀ. ማጠናከሪያ**

መምህር፤ ተማሪዎችዎን ዋና ዋና ነጥቦችን እንዲያብራሩ እና ጠቃሚ ነጥቦችን እንዲደግሙ ይጠይቁ።

**1.4.4. ምዘና እና ክትትል**

**ሀ. ምዘና**

ተማሪዎችን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ። ለምሳሌ፤

- ተማሪዎች ሃላፊነታቸውን እንዲዘረዝሩ ይጠይቁ።
- ተማሪዎች በቤተሰባቸው እና በማህበረሰባቸው ውስጥ ያላቸውን ኃላፊነት እንዲገልጹ ጠይቃቸው።
- ተማሪዎች ለሀገራቸው ስላላቸው ሀላፊነት የክፍል ስራ ይስጧቸው።

**ለ. ክትትል**

እርስ በርሳቸው፣ በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ እና በሀገር ደረጃ እንዲወያዩ እና ሃላፊነታቸውን እንዲያብራሩ ያበረታቷቸው።

**1.4.5. የትምህርት 4 ተግባራት መልስ**

**ተግባር 5**

1. ሦስቱ የኃላፊነት ደረጃዎች

ሀ. የግለሰብ ደረጃ ኃላፊነት

ለ. የቤተሰብና ማህበረሰብ ደረጃ ኃላፊነት

ሐ. የሀገራዊ ደረጃ ኃላፊነት

2. የግለሰብ ደረጃ ሃላፊነቶች

- በአክብሮት መናገር፤
- የሌሎችን ሀሳብ ማክበር፤
- የትምህርት ቤቶችን የጊዜ ሰሌዳዎች፣ ደንቦችን እና መመሪያዎችን መከተል፤
- መምህራን ሚሰጡንን የቤትና የክፍል ስራዎችን በወቅቱ ማጠናቀቅ፤
- ምግብን አለማባከን፤
- እውነትን መናገር፤
- አለመዋሸት፤
- የግል ንፅህናን መጠበቅ፤
- ለጓደኞች ታማኝ መሆን፤
- ከራስ ወዳድነት ወጥተን ሌሎችን መርዳት፤
- ጎጂ የሆኑ ቁሳቁሶችን አለመጠቀም፤
- ከታላላቆቻችን፣ ከቤተሰብ እና ከመምህራን ምክር መቀበል።

## 1.5. ትምህርት አምስት፤ የግብረገባዊ ኃላፊነት አይነቶች

**የተመደበ ክፍለ ጊዜ፡- 5**

### 1.5.1 ይዘቶች

- የተገባን ቃል መጠበቅ፣
- ሌሎችን መርዳት፣
- የሀብት አጠቃቀም፣
- የህዝብ ተሳትፎ፣
- ግብርን በጊዜ መክፈል፣
- የትራፊክ ህጎችን ማክበር
- ወዮማ

### 1.5.2 አጠቃላይ መግለጫ

ሰዎች በስነ ምግባር እና በሌሎች እሴቶች ተሳስረው አብረው የሚኖሩ እና እርስ በርስ የሚደጋገፉ ማህበራዊ ፍጥረታት ናቸው፡፡ ስለዚህ አንድ ግለሰብ ከሌሎች ጋር ያለው ግንኙነት ሃላፊነቱን ለመወጣት ባለው ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ተማሪዎችም የሞራል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

### 1.5.3 የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጓዴ ወረቀት / ወፍራም ወረቀት፣ ፎቶግራፎች፣ ካሴቶች፣ ፊልሞች፣ ስዕሎች፣ ግራፊክስ፣ ካርታዎች እና የመሳሰሉት፤

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

ስለተለያዩ የሞራል ሃላፊነቶች ተማሪዎችን ይጠይቋቸው፤ ተማሪዎችን በትናንሽ ቡድኖች ይከፋፍሏቸው እና ስለተለያዩ የሞራል ሃላፊነቶች እንዲወያዩ እና በክፍል ውስጥ ላሉ ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ያግዟቸው።

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

መምህር ስለ ስነምግባር ኃላፊነት ዓይነቶች ለማስተማር የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች አስቀድመው ያዘጋጁ፤ እነሱም፡- ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጓዴ ወረቀት ወደ ክፍል ውስጥ አምጥተው የትራፊክ መብራቶችን አሳዩ፡፡

**የትምህርት አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

መምህር፤ ተማሪዎችዎ ያለፉትን ትምህርቶች ያስታውሷቸው፤ የእለቱንም ትምህርት ያስተዋውቋቸው፡፡ ቃል መግባትን፣ ሌሎችን ስለመርዳት፣ ሃብትን በአግባቡ ስለመጠቀም፣ የህዝብ ተሳትፎ፣ ግብር መክፈልን፣ የትራፊክ ደንቦችን ስለማክበር እና አካባቢን ስለመጠበቅ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።

**ለ. የዝግጅት አቀራረብ**

የተሰፋ ቃል ስለ መፈጸም፣ ሌሎችን ስለመርዳት፣ ሀብትን በጥበብ ስለመጠቀም፣ የሕዝብ ተሳትፎ፣ ግብር ስለመክፈል፣ የትራፊክ ሕጎችን ስለማክበር እና አካባቢን ስለ መንከባከብ ያብራሩ።

**ሐ. ማጠናከሪያ**

መምህሩ፤ ተማሪዎችዎ ዋና ዋና ነጥቦቹን እንዲያብራሩ ይጠይቁ እና ሁሉንም አስፈላጊ ነጥቦች ይደግሙላቸው፡፡

**1.5.4. ምዘና እና ክትትል**

**ሀ. ምዘና**

ለምሳሌ ተማሪዎችን ጥያቄዎች መጠየቅ፤

የገቡትን ቃል የመፈጸም፣ ሌሎችን የመርዳት፣ ሃብትን በጥበብ የመጠቀም፣ የህዝብ ተሳትፎ፣ ግብር የመክፈል፣ የትራፊክ ህጎችን የማክበር እና አካባቢን የመንከባከብ ሀላፊነትህ/ሽ ምንድን ናቸው?

**ለ. ክትትል**

ተማሪዎች ስለቃል መግባትና ቃልን ስለማክበር፣ ሌሎችን ስለመርዳት፣ ሃብትን በጥበብ ስለመጠቀም፣ ስለየህዝብ ተሳትፎ፣ ግብር ስለመክፈል፣ የትራፊክ ህጎችን ስለማክበር እና አካባቢን ስለመንከባከብ እንዲወያዩ እና እንዲያብራሩ ያበረታቷቸው።

### 1.5.5. የትምህርት 5 ተግባራት መልስ

**ተግባር 6**

1. አዎ፣ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሃብቶችን የመጠበቅ ኃላፊነት አለብን፤ ተክሎችን መንከባከብ፣ ውሃን መቆጠብ፣ ልብስን በንጽህና መያዝ፣ መማርያ መጻህፍትን በጥንቃቄ መያዝ እና ወዘተ፤
2. ችግኞችን መትከልና መንከባከብ፣ በጎ አድራጎት ስራ ላይ መሳተፍ፣ መጽሃፍ ማንበብ እና ሌሎች…
3. የቤተሰብ ልምዳቸውን ያካፍሉ።

**ተግባር 7**

1. ተማሪዎች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ያድርጉ፤
2. በማህበረሰቡ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ያለባቸው ተግባራት፡-

ሀ. የአካባቢ ጽዳት፤

ለ. ለጎረቤቶች መላላክ፤

ሐ. የእፅዋት እንክብካቤ፤

መ. የተቸገሩ ሰዎችን መርዳት፤

ሠ. አድልዎ አለመስራት

3. ወደፊት በማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍ እንዲነሳሱ ያድርጉ!

**ተግባር 8**

1. ግራ እና ቀኝ ተመልክቶ ዜብራን መሻገር
2. አንድ ሰው ሊያከብራቸው የሚገቡ አንዳንድ የትራፊክ ደንቦች፡-

- በግራ አቅጣጫ መሄድ፤
- መንገድ ላይ አለመቆም፤
- በመንገድ ላይ ሲራመዱ አለመቸኮል፤
- የትራፊክ ምልክቶችን ማክበር፤
- ቀይ መብራት 'አቁም' ማለት እንደሆነ ማወቅ፤
- አረንጓዴው መብራት 'ሂድ' ማለት እንደሆነ ማወቅ፤
- የመኪናውን በር ከመክፈት በፊት አካባቢን መቃኘት፤

- አደባባይ ላይ መንገድ አለማቋረጥ፤
- እጅን በመኪና መስኮት አለማውጣት።

**ተግባር 9**

1. ወዩማ
2. ሀ. ለፈጣሪ

   ለ. ለሰው

   ሐ. ለመሬት

**1.6. የምዕራፍ 1 የክለሳ ጥያቄዎች መልስ።**

**ትዕዛዝ 1፡ 'እውነት' ወይም 'ሀሰት' ጥያቄዎችን መልሱ**

1. እውነት
2. ሀሰት
3. እውነት
4. ሀሰት
5. እውነት

**ትዕዛዝ 2፡ የምርጫ ጥያቄዎች መልስ**

1. መ
2. መ
3. መ

**ትእዛዝ 3**

1ኛ ጥያቄ

ሀ. ደሚቱ እህቷን ከትምህርት በኋላ የመውሰድ እና በሰዓቱ የመግባት ኃላፊነት አለባት።

ለ. ደሚቱ ሃላፊነቷን አልተወጣችም።በጊዜ ወደቤት ስላልገባች፤

ሐ. አዎ፣ እንደዚህ አይነት ጥፋት እንዳትደግም  ልትመከር ይገባል።

2ኛ ጥያቄ

ሀ. ቤት በሰዓቱ የመገኘት ኃላፊነት፤

ለ. አዎ፣ ሃላፊነቱን ተወጥቷል።

ሐ. አዎ፣ የበለጠ ኃላፊነት እንዲወስድ መበረታታት አለበት።

3ኛ ጥያቄ

ሀ. አያቷን የመርዳት ኃላፊነት አለባት።

ለ. አዎ፣ ሃላፊነቷን ተወጥታለች።

ሐ. አዎ፣ የበለጠ ኃላፊነት እንዲሰማት መበረታታት አለባት።

4ኛ ጥያቄ

ሀ. ጫልቱ ከብቶቿ ሲዲሳ እንዳይበሉ እና እንዳይሞቱ መጠበቅ ነበረባት፤

ለ. ሃላፊነቷን አልተወጣችም።

ሐ.አዎ፣ እንዲህ አይነት ጥፋት እንዳትደግም መመከር አለባት።

# ምዕራፍ ሁለት

# ጠንክሮ የመስራት ባህል

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች ውስጥ ስለጠንክሮ መስራት ባህል እና ስለአስፈላጊነቱ እንዲሁም ስለጠንክሮ መስራት መገለጫዎች ይማራሉ። በተጨማሪም የማንበብ ችሎታዎችን ለማዳበር የንባብ ልምዶችን እና ብልሃቶችን ይማራሉ፡፡

**ቁልፍ ቃላት እና ሐረጎች፤** ጠንክሮ የመሥራት ባህል፤ የልጅ መጎሳቆል፤ የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ፤ የንባብ ባህሪያት፤ የንባብ ስልቶች፤ የሙያ ክህሎቶች

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች**

**ከዚህ ትምርት በኋላ፡**

- የጠንክሮ መስራት ባህል ምንነት ያስረዳሉ፤
- የጠንክሮ መስራት ባህልን አስፈላጊነት ይገልጻሉ፤
- ጠንክሮ መሥራት ባህል ያለው ሰው ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፤
- የራሳቸውን ስራ እንዴት ማቀድ እንደሚችሉ ይገነዘባሉ፡፡

**ለምዕራፉ የተመደበ ክፍለ ጊዜ፡-** 20

**የትምህርት ይዘቶች**

ትምህርት 1፡ የጠንክሮ መስራት ባህል ምንነት

ትምህርት 2፡ ጠንክሮ የመስራት ባህል አስፈላጊነት

ትምህርት 3፡ የታታሪ ተማሪ የስራ ባህል መገለጫዎች

ትምህርት 4፡ የንባብ ባህል

ትምህርት 5፡ የማንበብ ባህልን የሚያዳብሩ ስልቶች

## 2.1.ትምህርት አንድ፡ የጠንከሮ መስራት ባህል ምንነት

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 3**

### 2.1.1. ይዘቶች

- የባህል ምንነት
- ጠንክሮ የመስራት ባህል ምንነት

### 2.1.2 አጠቃላይ መግለጫ

ባህል የሰው ልጅ ባህሪን እና በማህበራዊ ቡድኖች መካከል ያለውን ተግባር የሚመራ የህይወት እምነት፣ እሴቶች እና ሀሳቦች ስርዓት ነው። የተለያዩ የመማሪያ፣ የቋንቋ እና የባህል ቁሳቁሶችን ያካትታል። ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል፡፡ ባህል ሁለገብ ሃሳብ በውስጡ ስለሚይዝ ውስብስብ ነው፡፡ ጠንክሮ መሥራት ጊዜንና ጉልበትን መስዋዕት የማድረግ ልማድ ነው። ሥራ የማህበራዊ ኑሮ ወይም የሕይወት መሠረት ነው።

### 2.1.3 የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ገበታዎች፣ ሥዕሎች (ሰዎች ጠንክረው ሲሠሩ የሚሳይ ምስል)

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

ተማሪዎች በቡድን ሆነው ስለ ጠንክሮ መስራት ባህል በክፍል ውስጥ በቡድን ተወያይቶ እንዲያቀርቡ ማድረግ።

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

መምህር፤ የትምህርት እቅድ እና የመርጃ መሳርያዎችን ለምሳሌ የጠንክሮ መስራት ባህል ፎቶግራፎችን አዘጋጁ፡፡

**የትምህርት አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

መምህር፤ ያለፈውን ትምህርት ከከለሱ በኋላ የእለቱን ርዕስ ያስተዋውቁ። የእለቱን ትምህርት ከተማሪዎች የቀደመ ትምህርት እውቀት ጋር ማስተሳሰር ተማሪዎችን ለቀጣይ ስራ ያነሳሳል፡፡

## ለ. አቀራረብ

መምህር፤ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ትምህርቱን የበለጠ ውጤታማ ያድርጉ።

## ሐ. ማጠናከሪያ

ይህ ትምህርት ተማሪዎች መልካም ስነምግባር እንዲኖራቸው እና መመሪያዎችን እንዲከተሉ ያስችላቸዋል። ስለሆነም መምህር፤ ተማሪዎች የተማሩትን ዋና ዋና ነጥቦች እንዲከልሱ የድርጉ። መምህር፤ የተማሪዎችን አገላለጽ በመከተል ይምሯቸው።

## 2.1.4. ምዘና እና ክትትል

## ሀ. ምዘና

መምህር፤ ተማሪዎች በቡድን ሆኖው ስለባህል እና ስለጠንክሮ መስራት እንዲወያዩ በማድረግ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ።

## ለ. ክትትል

መምህር፤ የተማሪዎች እውቀትና ክህሎት በመገምገም፣ የተማሪዎች አስተሳሰብ እና ባህሪ መሻሻሉን በማረጋገጥ እና እራሳቸውን እንዲገመግሙ በማድረግ መከታተል ይችላሉ።

## 2.1.5. የትምህርት አንድ ተግባራት መልሶች

## ተግባር 1

1. የቤተሰባቸውን ጠንክሮ የመስራት ባህል ለምሳሌ እናታችን ልብስ ስታጥብ አባታችን ምግብ ያበስላል፣ እኔ ወንድሜና እህቴ ደግሞ ቤት እናጸዳለን፣ እቃ እናጥባለን ወዘተ...እንዲያካፍሉ ያድርጉ፡፡

2. ተማሪዎች የአካባቢያቸውን የስራ ባህል ለምሳሌ በደቦ መስራት፣ ስራን ያለጾታ ገደብ መስራ ወዘተ...እንዲገልጹ ያድርጉ።

3. እቅድ ማውጣት፣ ምርታማነትን መጨመር፣ ወዘተ…

4. በጠንክሮ መስራት፡፡ ጠንክሮ መሥራት የስኬት መነሻ እና መድረሻ ስለሆነ፡፡

## 2.2. ትምህርት ሁለት፡ የጠንክሮ መስራት ባህል አስፈላጊነት

**የክፍለ ጊዜ ብዛት፡ 4**

### 2.2.1 ይዘቶች

- የስራ ባህል በትምህርት ቤት
- የስራ ባህል በስራ ቦታ
- የስራ ባህል በማህበረሰብ

### 2.2.2. አጠቃላይ መግለጫ

ጠንክሮ ማንበብ፣ ማጥናት እና ጥንቃቄ ማድርግ ለሁሉም ይጠቅማል። ይህም ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች ለግባቸው ጠንክረው እንዲሰሩ ያደርጋል። እቅድ መኖሩ ተማሪዎችን በቁርጠኝነትና በትኩረት እንዲሰሩ ያደርጋል። የጠንክሮ መስራት ባህል በትምህርት ቤት እና በሌሎች የስራ ቦታዎች ሊኖር ይችላል። በትምህርት ቤት ያለህ ደካማ የስራ ባህል ተማሪዎችን ሊጎዳ ይችላል። ተማሪዎች ጠንክሮ የማጥናት ባህል ከሌላቸው ስኬታማ ላይሆኑ ይችላሉ። ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ውጪ የሚሰሯቸው ስህተቶች ሌሎች አካላትን ሊጎዱ እንዲሁም የሌሎች ሰዎች ስህተት ተማሪዎችን ሊጎዱ ይችላሉ።

### 2.2.3 የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ሰንጠረገዦች፣ ስእላዊ መግለጫዎች፣ ወዘተ የጠንክሮ መስራትን አስፈላጊነት ያሳያሉ።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ቃለ መጠይቆች፣ የቡድን ውይይቶች፣ ትረካዎች እና የጉዳይ ጥናቶች

## ቅድመ ትምህርት ዝግጅት

መምህር፤ የትምህርት እቅድ ማዘጋጀት አለቦት። እንዲሁም የጠንክሮ መስራት ባህልን አስፈላጊነት የሚያሳዩ ምሥሎች ወይም ሥዕሎች ያሉ የትምህርት መርጃ መሳርያ ማዘጋጀት አለቦት።

## የትምህርት አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

መምህር፤ ያለፈውን ትምህርት ከከለሱ በኋላ የትምህርት ሁለት ይዘቶችን ያስተዋውቁ።

### ለ. አቀራረብ

ይህ ትምህርት በመምህር ተማሪ የእርስ በርስ መስተጋብር ሊቀርብ ይችላል። መምህር፤ ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ የመርጃ መሳርያዎችን ይጠቀሙ።

### ሐ. ማጠናከሪያ

መምህር፤ ተማሪዎች ዋና ዋና ነጥቦችን እንዲከልሱ አስፈላጊ ነጥቦችን ሁሉ ያስታውሷቸው፡፡

## 2.2.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

የጠንክሮ መስራት ባህል አስፈላጊነት ምን እንደሆነ ተማሪዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ።

### ለ. ክትትል

በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ውስጥ የጠንክሮ መሥራት አስፈላጊነትን እንዲያዳብሩ የተማሪዎችን ውይይቶች በመከታተል ማበረታታት ይችላሉ።

## 2.2.5. የትምህርት ሁለት ተግባራት መልሶች

### ተግባር 2

1. ጠንክሮ የመስራት ባህል አስፈላጊነት የማህበረሰብን እሴቶች (ለምሳሌ በወዝ የመኖርንና የሌላን ያለመመኘትን እሴት) ለመጠበቅ እና ሀብትንና የሰው ሃይልን በአግባቡ ለመጠቀም ይረዳል፤ ።

2. አዎ፤ ጠንክሮ መስራት በጥያቄ ቁጥር 1 ስር የተጠቀሱትን ጠቀሜታዎች ስለሚያስገኝ ነው፡፡

3. የበለጠ ጠንክሮ ለመስራት እና ገቢ እንዲጨምር ያደርጋል። የተረጋጋ ማህበረሰብ ለመፍጠር...

## 2.3. ትምህርት ሶስት፡ የጠንካራ ተማሪ የስራ ባህል መገላጫዎች

**የክፍለ ጊዜ መጠን፡ 5**

### 2.3.1 ይዘቶች

- የጠንካራ ሰራተኞች መገላጫዎች
- ጥንክሮ የሚሰሩ ተማሪዎች መገላጫዎች
- ጊዜን በአግባቡ መጠቀም
- ለስራ እቅድ ማውጣት
- ትግበራ
- የመማር ምዘና

### 2.3.2 አጠቃላይ መግለጫ

ጠንክሮ መስራት ተማሪዎች ሊኖሯቸው የሚገባ ባህሪ ነው። ጠንክረው የሚሰሩ ተማሪዎች ለመማር፣ ችሎታቸውን ለመጠቀም እና ክህሎታቸውን ለማሻሻል የሚጥሩ ናቸው። እንዲህ አይነት ተማሪዎች ስህተታቸውን አምነው የሚያሻሽሉ ናቸው። ጠንክረው የሚሰሩ ተማሪዎች ስኬታማ ህይወት የመምራት እድል ያላቸው ናቸው። በትምህርት ቤት የሚያሳዩትን መልካም ባህሪ ለወደፊቱ በስራቸው ማሳየት እንዲችሉ እና የስራ ስነምግባርን እንዲከተሉ ያስችላቸዋል።

### 2.3.3 የመማር ማስተማር ሂደቶች

**የትምህርት መርጃ መሳርያዎች**

ሥዕሎች፣ ገበታዎች፣ ፊልሞች፣ ኦዲዮና የእይታ መርጃዎች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

የሚና ተውኔቶች፣ ትረካዎች፣ የቡድን ውይይቶች፣ ቃለመጠይቆች፣ ወዘተ…

## ቅድመ ትምህርት ዝግጅት

መምህር፤ የጠንካራ ሠራተኞችን ባህሪያት የሚገልጹ እንደ ሥዕሎች፣ የፊልም ቻርቶች፣ ወዘተ... የመሳሰሉ የመማሪያ እቅድ እና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ማዘጋጀት አለብዎት።

## የትምህርት አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

መምህር፤ ያለፈውን ትምህርት ከከለሱ በኋላ የጠንካራ ተማሪ የስራ ባህል መገለጫዎች ርዕስን ያስተዋውቁ። ይህም ተማሪዎች አዲስ እውቀት እንዲቀበሉ እና ቀድሞ የነበረውን እንዲያስታውሱ ይረዳል። ለዚህም ስዕሎችን፣ ቻርቶችን፣ ሞዴሎችን እና ትረካዎችን መጠቀም አለብዎት፡፡

### ለ. አቀራረብ

ይህ ትምህርት በመምህር እና በተማሪ መስተጋብር ይቀርባል። መምህር፤ ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ የተምህርት መርጃ መሳረያ መጠቀም ይኖርብዎታል። እንዲሁም ትምህርቱን ለማጎልበት አስፈላጊ ጥያቄዎችን መጠቀም ይኖርብዎታል።

### ሐ. ማጠናከሪያ

ተማሪዎች የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች እንዲያብራሩ ያድርጉ፤ እንዲሁም ተማሪዎቹ ያልደረሱባቸውን አስፈላጊ ነጥቦችን ይከልሱላቸው።

## 2.3.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

ስለጠንካራ ስራ ባህል ባህሪያት እና ስለ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ምንነት በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ።

### ለ. ክትትል

ተማሪዎች የተማሩትን ሲተገብሩ መከታተል፤ የተማሪዎችን እውቀትና ክህሎት መገምገም፣ የተማሪዎች የአስተሳሰብ ባህሪ መሻሻሉን ማረጋገጥ፣ የተማሪዎችን ጥረት በመከታተል እራሳቸውን እንዲገመግሙ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 2.3.5 የትምህርት ሶስት ተግባራት መልሶች

**ተግባር 3**

1. የጠንካራ ተማሪዎች ባህሪያት፡-

   ሀ. በማንኛውም ጊዜ በሰዓት በትምህርት ቤት መገኘት፤

   ለ. ማስታወሻ መያዝ፣ የቤት ስራ በትክክል መስራት፤

   ሐ. የቤት ሥራ በግዜው መስራት፤

   መ. ትምህርታቸውን በቅርበት መከታተል፣ ያልተረዱትን ጥያቄዎች መጠየቅ፤

   ሠ. በክበቦች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፤

   ረ. ከመምህሮቻቸው ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር፤

   ሰ. በመማር ሂደት ውስጥ በንቃት መሳተፍ፤

   ሸ. ከትምህርት ቤት ውጪም ጠንክሮ መስራት።

   ቀ. ማጥናት፣ ቤተሰብን በስራ ማገዝ፣ ከትምህርት ቤቱ የሚጠበቁትን ተግባራት ማከናወን፣ ወዘተ…

# 2.4. ትምህርት አራት፡ የንባብ ባህል

**የክፍለ ጊዜ መጠን፡ 4**

## 2.4.1 ይዘቶች

- የንባብ ልምዶች
- የንባብ ልምዶችን የሚያዳብሩ መንገዶች

## 2.4.2. አጠቃላይ መግለጫ

መምህር፤ ቋንቋን የማስተማር ስልት ማለት ተማሪዎች በትክክል እንዲናገሩ፣ እንዲጽፉ እና በትክክል እንዲያዳምጡ እና እንዲያነቡ ማድረግ ነው፡፡ ማንበብ ሁሉም ሰው በህይወቱ ማዳበር ያለበት ጥሩ ልማድ ነው፡፡ ማንበብ የቋንቋ ችሎታን እና የትርጓሜ ትምህርቶችን ለማዳበር ይረዳል፡፡ ከዚህ ሌላ ድብርትን እና ጭንቀትን ለመከላከል ይረዳል፡፡ ለአእምሮ ደህንነት በየቀኑ ቢያንስ ለጥቂት ደቂቃዎች ጥሩ መጽሐፍ ማንበብ አስፈላጊ ነው.

## 2.4.3 የመማር ማስተማር ሂደቶች

**የትምህርት መርጃ መሳርያዎች**

ሥዕሎች፣ ገበታዎች፣ ፊልሞች እና ኦዲዮ የእይታ መርጃዎች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

የሚና ተውኔቶች፣ ትረካዎች፣ የቡድን ውይይቶች፣ ቃለመጠይቆች፣ ወዘተ.

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

መምህር፤ የኢትዮጵያን ማህበረሰብ የማንበብ ልማዶች የሚገልጹ እንደ ሥዕሎች፣ የፊልም ቻርቶች፣ ወዘተ የመማሪያ እቅድ እና የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን ማዘጋጀት አለብዎት።

**የትምህርት አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

መምህር፤ ያለፈውን ትምህርት ከከለሱ በኋላ የንባብ ባህል ርዕስን ያስተዋውቁ። ይህም ተማሪዎች አዲስ እውቀት እንዲቀበሉ እና ቀድሞ የነበረውን

እንዲያስታውሱ ይረዳል። ለዚህም ስዕሎችን፣ ቻርቶችን፣ ሞዴሎችን እና ትረካዎችን መጠቀም አለብዎት፡፡

**ለ. አቀራረብ**

መምህር፤ ይህ ትምህርት በመምህር እና በተማሪ የነቃ ተሳትፎ ይቀርባል። ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን መጠቀም አለብዎት።

**ሐ. ማጠናከሪያ**

መምህር፤ ተማሪዎች የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች እንዲያብራሩ ያድርጉ፤ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ያልደረሱባቸውን አስፈላጊ ነጥቦች ይከልሱላቸው።

**2.4.4. ምዘና እና ክትትል**

**ሀ. ምዘና**

ተማሪዎችን የማንበብ ክህሎቶችን/ልማዶችን እንዴት ማዳበር እንደሚችሉ በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ።

**ለ. ክትትል**

ተማሪዎች የተማሩትን ሲተገብሩ መከታል፣ የተማሪዎችን እውቀትና ክህሎት መገምገም፣ የተማሪዎች አስተሳሰብ እና ባህሪ መሻሻሉን ማረጋገጥ እና የተማሪዎችን ጥረት በመከታተል እራሳቸውን እንዲገመግሙ ማድረግ ያስፈልጋል።

**2.4.5. የትምህርት አራት ተግባራት መልሶች**

**ተግባር 4**

1. ጥሩ የንባብ ባህል ለማዳበር፣ ለማንበብ ጊዜ መያዝ፣ ከፍላጎትና ከእድሜ ደረጃ አኳያ የሚሄዱ መጽሃፎችን ይዞ መገኘት፣ የንባብ ክበብ አባል ውስጥ መሳተፍ።

2. አንዳንድ የንባብ ጥቅሞች፡- እውቀት ለማግኘት፣ ለመዝናኛ፣ መረጃ ለማግኘት፣ ለችግር መፍትሔ ለማግኘት ናቸው።

3. ቀስበቀስ ንባብን መለማመድ፣ አለመስልቸት፣ ማንበቢያ ስፍራ መምረጥ፣ የአሳዳጊ ወይም የወላጅ እገዛ ማግኘት…

## 2.5 ትምህርት አምስት፡ የንባብ ባህልን የማስፋፋት ስልቶች

**የክፍለ ጊዜ መጠን፡ 4**

### 2.5.1 ይዘቶች

- የንባብ ስልቶች የሚማሩበት
- ውጤታማ ንባብ

### 2.5.2 አጠቃላይ መግለጫ

ጥሩ የንባብ ስልቶች ተማሪዎችን በብቃት እንዲያነቡ ይረዳቸዋል። የንባብ ስልቶች በመጠቀም ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ከማንበብ ትልቅ ውጤት ያገኛሉ። እነዚህ ስልቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡፡ ለአላማ ማንበብ፣ በጥልቀት ማንበብ፣ በፍጥነት ማንበብ፣ መረጃ ሰጪ ቃላት ማንበብ፣ በአረፍተ ነገር ማንበብ፣ መጽሃፎችን ምልክት ማድረግ፣ ማስታወሻ መያዝ እና ከሌሎች ጋር ማንበብ።

### 2.5.3. የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳርያዎች**

ሥዕሎች፣ ገበታዎች፣ ፊልሞች እና ኦዲዮ የእይታ መርጃዎች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

ሮል ሞዴሊንግ፣ ትረካዎች፣ የቡድን ውይይቶች፣ ቃለመጠይቆች እና የመሳሰሉት።

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

መምህር፤ የኢትዮጵያን ማህበረሰብ የንባብ ስልቶችን የሚገልፅ የመማሪያ እቅድ እና የትምህርት መርጃ መሳርያ እንደ ስዕል እና የመሳሰሉትን ማዘጋጀት አለብዎት።

## የትምህርት አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

መምህር፤ ያለፈውን ትምህርት ከከለሱ በኋላ የንባብ ስልት ርዕስን ያስተዋውቁ። ይህም ተማሪዎች አዲስ እውቀት እንዲቀበሉ እና ቀድሞ የነበረውን እንዲያስታውሱ ይረዳል። ለዚህም ስዕሎችን፣ ቻርቶችን፣ ሞዴሎችን እና ትረካዎችን መጠቀም አለብዎት፡፡

### ለ. አቀራረብ

ይህ ትምህርት በመምህር እና በተማሪ ተሳትፎ ይቀርባል። ትምህርቱን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳርዎችን ይጠቀሙ። እንዲሁም ትምህርቱን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ጥያቄዎችን መጠቀም ይኖርበታል።

### ሐ. ማጠናከሪያ

ተማሪዎች የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች እንዲያብራሩ ያድርጉ፤ በተጨማሪም ያልደረሱበትን አስፈላጊ ነጥቦች ይድግሙላቸው።

## 2.5.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

መምህር፤ የማንበብ ልምዶችን ለማዳበር የሚረዱ ስልቶች ላይ እንዲያተኩር እና እንዲወያዩበት የክፍል ስራ በመስጠት የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ።

### ለ. ክትትል

ተማሪዎች የተማሩትን ሲተገብሩ መከታተል፣ የተማሪዎችን እውቀትና ክህሎት መገምገም፣ የተማሪዎች አስተሳሰብ እና ባህሪ መሻሻሉን ማረጋገጥ እና የተማሪዎችን ጥረት በመከታተል እራሳቸውን እንዲገመግሙ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 2.5.5. የትምህርት 5 ተግባራት መልስ

### ተግባር 5

**1. የንባብ ባህልን ለማስፋፋት ቁልፍ ብልሃቶች**

- ለዓላማ ማንበብ
- መረጃ ሰጪ ቃላትን ማንበብ
- ማስታወሻ መያዝ

**2. ማንበብን ውጤታማ ለማድረግ ማድረግ ያለብን ነገሮች፡-**

ሀ. ለማንበብ ቦታ መምረጥ፣ ትክክለኛ ብርሃን እና ጸጥታ ያለው ቦታ መምረጥ አስፈላጊ ነው፣

ለ. በሚያነቡበት ጊዜ ጩኸት አለመፍጠር፣

ሐ. በዕረፍት ጊዜ እና ምቹ በሆነ ሁኔታ ማንበብ፣

መ. ምን እንደሚነበብ እና የሚነበብ ይዘትን መወሰን፤

ሠ. ለማንበብ በቂ ጊዜ እንዳለን ማረጋገጥ

**2.5.6. የምዕራፍ 2 የክለሳ ጥያቄዎች መልስ**

| ትእዛዝ 1፡ እውነት እና ሀሰት | ትዕዛዝ II: ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ |
|---|---|
| እውነት | መ |
| እውነት | ለ |
| ሀሰት | ሐ |
| እውነት | ሀ |
| ሀሰት | |

| ትዕዛዝ III: ባዶውን ቦታ ሙላ/ዪ | ትእዛዝ IV  አጭር መልስ ስጥ/ጪ። |
|---|---|
| 1. ጠንክሮ መስራት<br>2. ለዓላማ ማንበብ፣ መረጃ ሰጪ ቃላትን ማንበብ፣ ማስታወሻ መያዝ | በፍጹም። ምክንያቱም ጠንክረው እንዲሰሩ የምናስተምራቸው በልበ ሙሉነት መልካም ስራን ለመስራት ስለሚጠቅማቸው እና ወደፊትም ስኬት ስለሚያገኙ ነው። |

# ምዕራፍ ሦስት

# የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታ

## መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ትክክለኛ ውሳኔዎችን የመስጠት ችሎታን የሚመለከት ሲሆን አምስት የትምህርት ክፍሎች አሉት፤ እነሱም፡- የውሳኔ አሰጣጥ ፅንሰ ሀሳብ፣ ትክክለኛ ውሳኔዎችን የመወሰን ችሎታ፣ የትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች፣ ትክክለኛ ውሳኔዎችን የመስጠት አስፈላጊነት እና የትክክለኛ ውሳኔዎችን እንቅፋቶች ናቸው፡፡ የቡድን ውይይቶች፣ ማብራሪያዎች፣ ሠርቶ ማሳያዎች፣ ታሪክ መናገር፣ ተግባራዊ ክንዋኔዎች፣ ምልከታዎች፣ ጥያቄዎች እና የጽብረቃ ጽሑፎች ይህንን ትምህርት ለማቅረብ እንደ ዋና ዘዴዎች ተጠቁመዋል። በእያንዳንዱ ትምህርት ተማሪዎችን ለማበረታታት ጥያቄዎች እና ተግባራት ቀርበዋል።

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፡-**

**በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ተማሪዎች፡-**

- ➢ የውሳኔ አሰጣጥ ጽንሰ ሃሳቦችን ይረዳሉ፤
- ➢ ትክክለኛ ውሳኔዎችን የመስጠት ችሎታ ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፤
- ➢ ዋጋ ያለው ውሳኔ ይሰጣሉ፤
- ➢ ትክክለኛውን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ያሳያሉ፤
- ➢ ትክክለኛ ውሳኔዎችን ለማድረግ እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን ይለያሉ፡፡

**ትምህርቶች፡-**

- ትምህርት 1፡ የትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ጽንሰ ሃሳብ
- ትምህርት 2፡ የትክክለኛ ውሳኔ ችሎታዎች ባህሪያት
- ትምህርት 3፡ ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት መከተል ያለብን እርምጃዎች
- ትምህርት 4፡ የትክክለኛ ውሳኔ አስፈላጊነት
- ትምህርት 5፡ የትክክለኛ ውሳኔ እንቅፋቶች

**ለምዕራፉ የተመደበ ክፍለጊዜ ብዛት፡ 20**

## 3.1. ትምህርት አንድ፡ የትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ጽንሰ ሀሳብ

**የክፍለ ጊዜ መጠን፡ 3**

### 3.1.1. ይዘት

- ውሳኔ መስጠት

### 3.1.2. አጠቃላይ መግለጫ

የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታ ተማሪዎች ማግኘት ያለባቸው ቁልፍ ክህሎት ነው። ውሳኔ መስጠት ማለት ካሉ አማራጮች መካከል በምዘና የተሻለውን አማራጭ የመወሰን/የመምረጥ ሂደት ነው። ለምሳሌ ተማሪዎች የሚወስዷቸው ውሳኔዎች በስኬታቸው ላይ ተጽዕኖ አለው። የተማሪዎች ግንኙነት እና ስኬት በአብዛኛው በውሳኔ ላይ ይመሰረታል።

### 3.1.3. የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳርያዎች**

ገበታዎችን፣ ፎቶዎችን፣ ቪዲዮዎችን፣ ፊልሞችን፣ መጽሔቶችን፣ ብሮሸሮችን ፣ ንድፎችን፣ ግራፎችን፣ ፖስተሮችን፣ የፎቶ ግራፎችን፣ ካርታዎችን፣ ምሳሌዎችን እና ወዘተ…

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

መምህር፤ በክፍል ውስጥ የሚከተሉትን የመማር እና ማስተማር ዘዴዎችን መጠቀም ይችላሉ።

- የግንዛቤ ጥያቄዎች
- የጉዳይ ጥናት
- መግለጫ
- ቃለ ምልልስ

- የቡድን ውይይት

## ቅድመ ትምህርት ዝግጅት

መምህር፤ በዚህ ትምህርት ውስጥ ተማሪዎችን ሊያግዙ የሚችሉ ዋና ዋና ጉዳዮችን ያዘጋጁ፡፡ በተጨማሪም በዚህ ርዕስ ላይ ተገቢውን መጽሐፍ በማንበብ በቂ ዝግጅት አድርጉ። ስለ ውሳኔ አሰጣጥ ተማሪዎችን ለማስተማር አስፈላጊ ዝግጅት ያድርጉ፡፡

## የትምህርት አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን ይጀምሩ፡፡

- ተማሪዎች ከስእል 3.1 ምን መለከታለህ/ቻለሽ?
- ውሳኔ ምን ማለት ነው?

### ለ. አቀራረብ

የውሳኔ አሰጣጥን ምንነት ማብራራት እና ምሳሌዎችን መስጠት ይችላሉ።
ተማሪዎች ምን አይነት ውሳኔዎችን ማድረግ እንዳለባቸው በማብራራት ትምህርትዎን መጀመር ይችላሉ።

### ሐ. ማጠናከሪያ

ተማሪዎችን በውሳኔ አሰጣጥ ባህሪ ውስጥ የተዘረዘሩትን ቁልፍ ሀሳቦች በማስታወስ የእለቱን ትምህርት ማጠናከር ይችላሉ።

## 3.1.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

የተጣመሩ የክፍል ስራ ጥያቄዎች ለምሳሌ ከስእል 3.1 ምን ታያለህ/ሽ?
ተማሪዎች አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሟቸው ምን ዓይነት ውሳኔዎችን ያደርጋሉ?

ለ. ክትትል

የተማሪዎችን ግንዛቤ በመከታተል እንዴት ውሳኔ እንደሚያደርጉ በማሳየት እንዲያሳዩዋቸው እና እንዲረዱቸው እና ወደ ኋላ ተመልሰው ዋና ዋና ጉዳዮችን እንዲወያዩባቸው ማበረታታት ይችላሉ።

3.1.5. የትምህርት አንድ ተግባራት መልስ

ተግባር 1

ሀ. በፍጥነት የወደቁትን አዛውንት የበለጠ እንዳይጎዱ እገዛ ማድረግ፣ በአካባቢ ያሉ ሰዎች እንዲረዱቸው መጥራት፣ ከተቻለም ወደ ሀኪም ቤት ማድረስ ወዘተ... በተጨማሪም ለዚህ ተግባር የተማሪችዎን ሌሎች ምላሾች መቀበል።

ለ. አዎ ወይም አይ ብለው እንዲመልሱና ለመልሶቻቸው አሳማኝ ምክንያት እንዲሰጡ ማበረታታት፤

ተግባር 2

1. ስድስት ዓይነት ውሳኔዎች ተደርገዋል፡፡

ሀ. አንበሳው የጅቡን ጥጃ ለመውሰድ የወሰነው ውሳኔ፣

ለ. አንበሳና ጅብ  እንስሳት እንዲያስታረቋቸው የወሰኑት ውሳኔ፣

ሐ. እንስሳት ጥጃው የአንበሳው እንደሆነ የወሰኑት ውሳኔ፣

መ. ጦጢት በሬ እንደማይወልድ የወሰነችው ውሳኔ፣

ሠ. አንበሳው ዛፍ ላይ ወጥቶ ጦጢትን ለመግደል የወሰነው ውሳኔ፣

ረ. እንስሳት ጅቡን ይቅርታ ለመጠየቅ የወሰኑት ውሳኔ፤

2. ፍራቻ (አንበሳን መፍራት)

3. ተማሪዎች የየራሳቸውን ልምድ መነሻ በማድረግ የሚመልሷቸው የተለያዩ መልሶች፤

4. ትክክለኛ ውሳኔዎችን የማድረግ ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች መካከል

እብሪት (ለምሳሌ የአንበሳ) እና ፍራቻ (ለምሳሌ እንስሳት) ይጠቀሳሉ፡፡

## 3.2. ትምህርት 2፡ የትክክለኛ ውሳኔ ችሎታዎች ባህሪያት

**የክፍለ ጊዜ መጠን፡ 3**

### 3.2.1. ይዘቶች

- በጥልቀት ማሰብ
- ምክንያታዊ
- ሚዛናዊ ውሳኔ መስጠት

### 3.2.2. አጠቃላይ መግለጫ

መምህር፤ ተማሪዎችዎ ለሁሉም ሰው ጥሩ ውጤት የሚያመጣ ትክክለኛ ወይም ትክክለኛ የስነምግባር ውሳኔ እንዲወስኑ ይርዷቸው፤ ውሳኔያቸውም በጥልቅ ማሰብ፣ ምክንያታዊነት እና ሚዘናዊነት ባህሪያትን የሚሟላ እንዲሆን ይጠበቃል።

### 3.2.3 የመማር ማስተማር ሂደቶች

**የትምህርት መርጃ መሳርያዎች**

ገበታዎችን፣ ፎቶዎችን፣ ቪዲዮዎችን፣ መጽሔቶችን፣ ብሮሹሮችን፣ ንድፎችን፣ ግራፎችን፣ ፖስተሮችን ፎቶግራፎችን፣ ካርታዎችን፣ ሥዕሎችን፣ ካርቱን እና ሌሎችንም ይጠቀሙ።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

መምህር፤ የሚከተሉትን የመማር ማስተማር ዘዴዎች መጠቀም ይችላሉ፤

- የግንዛቤ ጥያቄዎች
- ትምህርቱን ማብራራት
- መግለጫ
- ጥያቄዎችን መጠየቅ
- የቡድን ውይይት

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

መምህር፤ በትምህርቱ ሂደት ዋና ዋና ይዘቶችን ማደራጀት እና አስፈላጊዎችን በማስታወሻ መያዝ ይጠበቅብዎታል፡፡

## የትምህርት አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን ይጀምሩ፤

- በቤት ውስጥ ትክክለኛ ውሳኔዎችን የማድረግ ልምድ አለህ/ሽ?
- ውሳኔህን/ሽን ሞራላዊ የሚያደርገው ምንድን ነው?

### ለ. አቀራረብ

**ትክክለኛ ውሳኔዎችን የማድረግ ችሎታ**

- በጥልቀት ማሰብ
- ምክንያታዊነት
- ሚዛናዊ ውሳኔ ማድረግ

### ሐ. ማጠናከሪያ

- ተማሪዎች የትምህርቱን ዋና ነጥቦችን እንዲያሳዩ ጠይቋቸው እና የእለቱን ትምህርት ለማጠናከር ጠቃሚ ነጥቦችን ይከልሱ።

## 3.2.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት እንዲረዱት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይችላሉ።

- ትክክለኛ ውሳኔ ማለት ምንድን ነው?
- በጥልቀት ማሰብ ምንድን ነው?
- ምክንያታዊነት ምን ማለት ነው?
- ሚዘናዊ ውሳኔ ምንድን ነው?
- በአስተያየቱ መሰረት የተማሪውን ትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ፣ በጥልቀት ማሰብ ፣ ምክንያታዊነት እና ሚዛናዊነት ከግንዛቤ በማስገባት መገምገም ያስፈልጋል።

**ለ. ክትትል**

ተማሪዎችዎ የትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ባህሪያትን እንዲረዱ እና በቁልፍ ጉዳዮች እንዲወያዩ በማበረታታት የተማሪዎችን ተግባራት መከታተል ይችላሉ።

**3.2.5.የትምህርት ሁለት ተግባራት መልሶች**

**ተግባር 3**

በእቅድ ያለመመራት፣ ስራን መወዘፍ፣ ኃላፊነትን አለመወጣት፣ ቸልተኝነት፣ ሊያጋጥም የሚችል ችግር ቀድሞ አለመገመት ...

## 3.3. ትምህርት 3፡ ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ደረጃዎች

**የክፍለ ጊዜ መጠን፡ 6**

### 3.3.1. ይዘቶች

1. ችግሩን መለየት
2. ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮችን ማስቀመጥ
3. በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚደርስ ተጽእኖን መለየት
4. ውሳኔ መስጠት እና መከታተል
5. ውሳኔን መከለስ (ውጤቶቹን መመዘን)።

### 3.3.2. አጠቃላይ መግለጫ

የውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች ችግር መለየት፣ መረጃ መሰብሰብ እና ለችግሩ መፍትሄዎችን ማምጣትን ያጠቃልላል። ተማሪዎች የውሳኔ አሰጣጥን ሂደት ደረጃዎችን ሲከተሉ፣ መማር እና ጥንቃቄ የተሞላበት ውሳኔዎችን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

### 3.3.3. የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳርያዎች**

ገበታዎችን፣ ፎቶዎችን፣ ቪዲዮዎችን፣ ፊልሞችን፣ መጽሔቶችን፣ ብሮሹሮችን፣ ንድፎችን፣ ግራፎችን፣ ፖስተሮች፣ ፎቶግራፎችን፣ ካርታዎችን፣ የካርቱን ምስሎችን እና ሌሎችንም መገልገል ይችላሉ።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ጥሩ ውሳኔዎችን ለማድረግ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ተማሪዎችን ጥያቄዎችን ይጠይቁ።

- ችግር መለየት
- ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮችን ማስቀመጥ
- በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚደርስ ተጽእኖን መለየት።
- ውሳኔ መስጠትና መከታተል።
- ውሳኔን መከለስ (ውጤቶቹን መመዘን)።

## ቅድመ ትምህርት ዝግጅት

መምህር፤ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ስለሚጠበቁ ሥነ ምግባራዊ ድርጊቶች ተማሪዎችን ለማስተማር አስፈላጊ ዝግጅት ያደርጉ፡፡

በትምህርቱ ሂደት ዋና ዋና ይዘቶችን በማደራጀትና አጭር ማስታወሻ በመያዝ መዘጋጀት ይችላሉ፤ በርዕሱ ላይ የሚረዳዎትን መጽሃፎች በማንበብ ይዘጋጁ፡፡

## የትምህርት አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን መጀመር ይችላሉ፤

- ችግር መለየት ምን ማለት ነው?
- ያሉ አማራጮች ማዘጋጀት ምን ማለት ነው?
- በውሳኔ አሰጣጥ የሚደርሱ ተጽእኖዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
- ውሳኔ መስጠትና መከታተል ለምን ይጠቅማል?
- ውሳኔን የመከለስ አላማ ምንድን ነው?

### ለ. አቀራረብ

የትክክለኛ ውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎችን ማብራራት

- ችግር መለየት
- ያሉ አማራጮችን መዘርዘር
- በውሳኔ አሰጣጥ የሚደርስ ተጽእኖን መለየት።

- ውሳኔ መስጠትና መከታተል።
- ውሳኔን መከለስ (ውጤቶቹን መመዘን)።

### ሐ. ማጠናከሪያ

መምህር፣ ተማሪዎች የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች እንዲያቀርቡ ይጠይቁ፣ ከዚያም ሁሉንም ተዛማጅ የሆኑትንና ያልሆኑትን በመገምገም መከለስ ይችላሉ።

## 3.3.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለተማሪዎች በመጠየቅ መገምገም ይችላሉ፡፡

- ያለን ችግርን መለየት ማለት ምንድን ነው?
- አማራጮችን ማዘጋጀት ማለት ምንድን ነው?
- የውሳኔ አሰጣጥ ተፅእኖ መለየት ማለት ምንድን ነው?
- ውሳኔ አሰጣጥና ክትትል ማለት ምንድን ነው?
- ውሳኔህን መከለስ (ውጤቱን መገምገም) ማለት ምንድን ነው?

### ለ. ክትትል

ጥሩ የውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎችን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚችሉ ለተማሪዎች ማሳየት እና ማበረታታት።

የቡድን ውይይቶችን እና መግለጫዎችን ለመላው ክፍል ተማሪዎች እንዲያደርጉ እርዷቸው።

## 3.3.5. የትምህርት ሶስት ተግባር መልሶች

### ተግባር 4

1. ብስኩት እንዲገዙ ጠየቀው፣ ልክ አልነበረም፡፡
2. ውሳኔ ላይ ለመድረስ ተቸገረ፡፡
3. ተማሪዎች የሚሰጧቸው የተለያዩ መልሶች፣

## 3.4. ትምህርት 4፡ ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነት

**የክፍለ ጊዜ መጠን፡ 3**

### 3.4.1 ይዘት

- **ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነት**

### 3.4.2. አጠቃላይ መግለጫ

መምህር፤ ለተማሪዎችዎ ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነትን በዝርዝር እንዲወያዩበት ያግዟቸው። ተማሪዎች ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነትን ከተረዱ ጥንቃቄ የተሞላበት ውሳኔዎችን ማድረግ ይችላሉ።

### 3.4.3. የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳርያዎች**

ገበታዎችን፣ ፎቶዎችን፣ ቪዲዮዎችን፣ ፊልሞችን፣ መጽሔቶችን፣ ብሮሹሮችን፣ ንድፎችን፣ ግራፎችን፣ ፖስተሮችን፣ .ፎቶግራፎችን፣ ካርታዎችን፣ ሥዕሎችን፣ ካርቱን እና ሌሎችንም ይጠቀሙ።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- ስለ ጥሩ ውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች ተማሪዎችን በሃሳብ የሚያነቡ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።
- ትንሽ ቡድን በመመስረት በስእል 3.1 ላይ ተወያዩ እና ምላሻቸውን ለሁሉም ክፍል አቅርቡ።

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

ተማሪዎችን ስለ ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነት ክህሎት ለማስተማር የተለያዩ መጽሃፎችን በማንበብ አስፈላጊውን ዝግጅት ማዘጋጀት ይችላሉ።

## የትምህርት አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን ይጀምሩ፡፡

- ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነት ምንድነው?

### ለ. አቀራረብ

- በዚህ ትምህርት፣ ተማሪዎች ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነት እንዲገነዘቡ በጥንቃቄ መምራት አለብዎት።
- በተጨማሪም ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት ለግለሰብ እና ለህብረተሰብ ያለውን ጠቃሚነት ማስረዳት አለብዎት፡፡

### ሐ. ማጠናከሪያ

ዋና ዋና ሃሳቦችን በመገምገም የጥሩ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት አስፈላጊነት ላይ አጽንኦት ይስጡ፡፡

## 3.4.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት እንዲረዱት፣ የክፍል ስራዎችን፣ ፈተናዎችን በመስጠት ወይም ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት ሀሳቦችን እንዲለዋወጡ እና የመልካም ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን በተለያዩ ምሳሌዎች እንዲወያዩ በማድረግ መገምገም ይችላሉ። በዚህ መሠረት ጥሩ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት አስፈላጊነትን በተመለከተ የተማሪዎችን ግንዛቤ ይገምግሙ።

በትምህርቱ መጨረሻ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ በመማር ሂደቱ የተማሪዎች ችሎታ መሻሻሉን ይገምግሙ፡፡

1. በአነስተኛ ደረጃ ማሰብን የሚጠይቁ ምን አይነት ውሳኔዎች ናቸው?
2. ጥልቅ ማሰብን የሚፈልጉ ውሳኔዎች ምን አይነት ናቸው?
3. አንዳንድ ውሳኔዎችን ከሌሎቹ የበለጠ አስፈላጊ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

**ለ. ክትትል**

**ተማሪዎች ትክክለኛ የማመዛዘንን አስፈላጊነት እንዲያሳዩ እና እንዲወያዩ ማበረታታት ይችላሉ። የቡድን ውይይት እንዲያደርጉ እና አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ በመርዳት መላውን ክፍል ያሳትፉ።**

**3.4.5. የትምህርት 4 ተግባራት መልስ**

**ተግባር 5**

1. አዎ/አይ በማለት ተማሪዎች የሚሰጧቸው ምክንያታዊ መልሶችን ይቀበሉ፤
2. እንደ ሁኔታው፣ እንደ ጊዜ እና እንደ ጉዳዩ ክብደት አንዳንድ ውሳኔዎች ከሌሎቹ የበለጠ አስፈላጊ ሊሆኑ ይችላሉ፤

## 3.5. ትምህርት 5፡ የትክክለኛ ውሳኔ እንቅፋቶች

### የክፍለ ጊዜ መጠን፡ 5

### 3.5.1. ይዘቶች

- አንድ ሰው ለራሱ ያለው አመለካከት
- ይሉኝታ
- የእኩዮች ተጽእኖ
- የቤተሰብ ፍላጎት
- ማህበራዊ ተጽእኖ
- የመረጃ ቅልጥፍና
- የአንድን ሰው አስተያየት ለመደገፍ መረጃዎችን ማበላለጥ፣

### 3.5.2. አጠቃላይ መግለጫ

ውሳኔ ለመስጠት ችግር በሚያጋጥም ጊዜ፣ ስሜታዊ ሳይሆኑ ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት  መጣር ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ስሜታዊ የሆኑ ሰዎች በፍጥነት ስለሚወስኑ ጥሩ ውሳኔን ለመስጠት ይቸገራሉ፡፡

### 3.5.3 የመማር ማስተማር ሂደት

### የትምህርት መርጃ መሳርያዎች

ገበታዎችን፣ ፎቶዎችን፣ ቪዲዮዎችን፣ ፊልሞችን፣ መጽሔቶችን፣ ብሮሹሮችን፣ ሥዕላዊ መግለጫዎችን፣ ግራፎችን፣ ፖስተሮችን፣ ፎቶግራፎችን፣ ካርታዎችን፣ ሥዕሎችን፣ ካርቱኖችን መገልገል ይችላሉ።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት እንቅፋቶችን በተመለከተ ተማሪዎችን ጥያቄ ይጠይቁ።

ፒራሚድ አሳታፊ የመማር ዘዴን ይጠቀሙ። (ፒራሚድ ከግለሰብ በመጀመር ወደ መላው ቡድን የሚኬድበት የማስተማር ዘዴ ነው)

ለተማሪዎችዎ "ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት እንቅፋቶች" የሚለውን ርዕስ ይስጧቸውና ለየብቻ ለሁለት ደቂቃ እንዲያስቡ ጊዜ ይስጧቸው።

በመቀጠል፣ በጥንድ የፃፉትን እንዲያወዳድሩ ያድርጉ። በዚህም ተማሪዎች አዲስ ወይም ተመሳሳይ መልስ እንዳላቸው ያረጋግጡ። ከዚያም በቡድናቸው መልሶቻቸውን በማወዳደር እንዲወያዩ ያድርጉ።

በመጨረሻም ከመላው ክፍል አስተያየቶችን ያግኙ። ሁሉም ቡድን ምላሽ ሊሰጥህ አይገባም። ይልቁንስ በቡድናቸው የተነሱትን ጠቃሚ ነጥቦች ለማካፈል የተወሰኑ ቡድኖችን ይምረጡ። የተፈቱ ችግሮችን ቢያንስ ከሶስት ቡድኖች በመውሰድ መልሶችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ያስፍሩ።

## ቅድመ ትምህርት ዝግጅቶች

ጥሩ ውሳኔዎችን የማድረግ ተግዳሮቶችን ለተማሪዎች ለማስተማር አስፈላጊ ዝግጅት።

## የትምህርት አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

ያለፈውን ትምህርት በመከለስ ጥሩ ውሳኔዎች በመስጠት ሂደት ስላጋጠሙ ተግዳሮቶች የግንዛቤ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ትምህርቱን ይጀምሩ።

**ለ. አቀራረብ**

መምህር፤ ለተማሪዎችዎ ጥሩ ውሳኔዎችን በመስጠት ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችን ለምሳሌ ስለራስ ያለ አመለካከት፣ መተሳሰብ፣ የእኩዮች ጫና፣ የቤተሰብ ጫና፣ ማህበራዊ ጫና፣ መረጃን በማበላለጥ ማዳላት እና የመሳሰሉትን ያብራሩላቸው፡፡

**ሐ. ማጠናከሪያ**

ጥሩ ውሳኔዎችን የማድረግ ዋና ዋና ችግሮችን በመገምገም ለተማሪዎች ማስረዳት አለብዎት፡፡ ተማሪዎቹ የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች እንዲጠቁሙ ጠይቋቸው፡፡ ከዚያም ተማሪዎች በጥቆማቸው ያላካተቱትን አስፈላጊ ነጥቦች በማስታወስ ትምህርቱን ያጠናቁ፡፡

**3.5.4. ምዘና እና ክትትል**

**ሀ. ምዘና**

በትምህርቱ መጨረሻ የማስተማር ሂደቱን ለማሻሻል የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተማሪዎችዎን ይጠይቁ፡፡

1. አንድ ሰው ለራሱ ያለው አመለካከት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?
2. ይሉኝታ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?
3. የእኩዮች ተጽዕኖ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?
4. የቤተሰብ ጫና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?
5. ማህበራዊ ጫና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?

**ለ. ክትትል**

ተማሪዎች ትክክለኛ ውሳኔዎችን የማድረግ ችግሮች ላይ በቡድናቸው እንዲወያዩ አበረታቷቸው። የውይይቱንም ውጤት ለሁሉም የክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ አግዟቸው።

### 3.5.5. የትምህርት 5 ተግባራት መልሶች

**ተግባር 6**

1. የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን ከሚያደናቅፉ ነገሮች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

ሀ. አንድ ሰው ለራሱ ያለው አመለካከት

ለ. ይሉኝታ

ሐ. የእኩዮች ተጽዕኖ

መ. የቤተሰብ ፍላጎቶች

ሠ. ማህበራዊ ተጽእኖ

ረ. የመረጃ ብቃት

ሰ. የአንድን ሰው አስተያየት ለመደገፍ ሲባል መረጃን ማበላለጥ

2. ተማሪዎች ጥሩ ውሳኔዎችን እንዳይሰጡ እንቅፋት የሚሆኗቸውን ማናቸውንም ልምዶች እንዲገልጹ ያበረታቷቸው፡፡

## 3.6. የምዕራፍ 3 የክለሳ ጥያቄ መልስ

መምህር፤ ግለሰቦች የተለያዩ ውሳኔ የሚሰጡባቸውን ጉዳዮች ተማሪዎችዎ እንዲጠቁሙና እና በጉዳዮቹ ላይ ማብራሪያ እንዲያቀርቡ ያበረታቷቸው።

# ምዕራፍ 4

# የአካባቢ እንክብካቤ

## መግቢያ

በዚህ ምእራፍ ስለአካባቢ እንክብካቤ ፅንሰ ሀሳብ፣ ስለአካባቢ እንክብካቤ ፋይዳዎች፣ አካባቢን ስለመጠበቅ መንገዶች እና አካባቢን ባለመንከባከብ ምክንያት የሚደርሱ ጉዳቶችን እናነሳለን።

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፡-**

**በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ተማሪዎች፡-**

- የአካባቢ እንክብካቤ ምንነትን ያብራራሉ፤
- አካባቢን የመንከባከብ ጥቅሞችን ያደንቃሉ፤
- አካባቢን የመጠበቅ መንገዶችን ይገልጻሉ፤
- አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትለውን ችግሮችን ይዘረዝራሉ።

**ትምህርቶች፡-**

ትምህርት 1: የአካባቢ ምንነት

ትምህርት 2፡ የአካባቢ እንክብካቤ ምንነት

ትምህርት 3፡ የአካባቢ እንክብካቤ አስፈላጊነት

ትምህርት 4፡ አካባቢን የመንከባከብ መንገዶች

ትምህርት 5፡ አካባቢን ባለመንከባከብ የሚደርስ ጉዳት

**ለምዕራፉ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ 20**

# 4.1. ትምህርት 1፡ የአካባቢ ምንነት

**የክፍል ጊዜ መጠን 3**

## 4.1.1. ይዘቶች

- **የአካባቢ ምንነት**

## 4.1.2. አጠቃላይ መግለጫ

አካባቢ የሚለው ቃል የተለያየ እና ሰፊ ትርጉሞች አሉት። አንዳንድ ሰዎች 'አካባቢ' የሚለውን ቃል በአጭሩ 'ተፈጥሮ' በማለት ይተረጉሙታል። በሌላ በኩል ደግሞ የመሬት አቀማመጥ፣ የተፈጥሮ ባህርያትን እና ሂደቱን እንዲሁም የሰው ልጅ የሆኑትንና ያልሆኑትን ሁሉ አካባቢ በማለት ይተረጉሙታል፡፡ ሌሎች ደግሞ በተወሰነ መልኩ የሰው ልጅ ጉዳዮችን የሚያካትት ነው ይላሉ። ብዙ ሰዎች የግብርና እና ለከብት እርባታ የሚውል ሰፊ መሬትን የአካባቢ አካል አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ሌሎች ምሁራን ደግሞ ይህንን ሀሳብ በማስፋት ሁሉንም የመሬት ገጽታዎችን እና ከተማን ጨምሮ አካባቢ በማለት ይጠሩታል።

## 4.1.3 የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ገበታዎች፣ ፎቶዎች፣ ቪዲዮዎች፣ ፊልሞች፣ መጣጥፎች፣ ብሮሸሮች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ግራፎች፣ ፖስተሮች፣ የፎቶግራፍ ግራፎች፣ ካርታዎች፣ ሥዕሎች፣ መጽሔቶች እና ጋዜጦች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

የቡድን ውይይት፣ ክርክር፣ ሚና መጫወት፣ ድራማ፣ ቃለ መጠይቅ

**ለቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

በኢትዮጵያ እና በሌሎችም አካባቢዎች የአካባቢ ጥበቃን አስፈላጊነት የሚያሳዩ የትምህርት እቅዶችን እና ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ፡፡

## የትምህርቱ አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

ያለፈውን ትምህርት በአጭሩ ከልሰው የእለቱን ትምህርት ርዕስ ያስተዋውቁ። የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ከአዲሱ ትምህርት ጋር በማዛመድ የተማሪዎችን ፍላጎት ከፍ ያድርጉ። በተጨማሪም ስዕሎችን፣ ገበታዎችን፣ ሞዴሎችን እና ታሪኮችን ማሳየት ይችላሉ። ይህም የተማሪዎች ተነሳሽነት እንዲጨምር እና ትምህርቱ ተጨባጭ እንዲሆን ያግዝዎታል።

### ለ. አቀራረብ

መምህር፤ በዚህ ክፍል ለተማሪዎችዎ የትምህርቱን አላማ በማብራራት እንዲሳተፉ አግዟቸው፤ እንዲሁም ከአዳዲስ መረጃዎች ጋር አስተዋውቋቸው፣ ከዚያም የእለቱን ትምህርት ያቅርቡላቸው። ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ፣ የተለያዩ የመማሪያ ቁሳቁሶችን በመጠቀም፣ መረዳታቸውን የሚገመግሙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና ከተማሪዎች ግብረ መልስ ማግኘት መቻል አለብዎት።

### ሐ. ማጠናከሪያ

መምህር፤ የእርስዎ ዋና ተግባር ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማገዝ ይሆናል። ለዚህም የእለቱን ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦች በጥያቄ መልክ አቅርቡላቸው። የተማሪዎች ምላሽ ያልተሟላ ወይም የተሳሳቱ ከሆኑ ያርሙዋቸው።

## 4.1.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

ተማሪዎችን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ። ምሳሌ፡ አካባቢ ማለት ምን ማለት ነው?

### ለ. ክትትል

ተማሪዎችን አዳዲስ ፅንሰሀሳቦችን እና ክህሎቶችን ሲተገብሩ፣ የተማሪዎችን ዕውቀት እና ክህሎቶች ይከታተሉ። ተማሪዎች አስተሳሰባቸውን ወይም

ባህሪያቸውን እንደለወጡ የሚያሳይ ማስረጃ ይፈልጉ። በተጨማሪም በቡድን የላቸውን ተሳትፎ ይከታተሉ።

### 4.1.5. የትምህርት 1 ተግባራት መልስ

**ተግባር 1**

1. አካባቢ ሁሉንም የሰው እና የሰው ልጅ ያልሆኑ (በምድር ውስጥ እና ውጪ) መልክዓ ምድራዊ ባህሪያት እና ተፈጥሯዊ ሂደቶችን ያጠቃልላል፡፡

## 4.2. ትምህርት 2፡ የአካባቢ እንክብካቤ ምንነት

የክፍለ ጊዜ መጠን 4

### 4.2.1. ይዘት

- **የአካባቢ እንክብካቤ ምንነት**

### 4.2.2 አጠቃላይ መግለጫ

አካባቢን መጠበቅ አካባቢያችንን ለኑሮ ምቹ ለማድረግ የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ ያጠቃልላል። ለምሳሌ ዛፎችን መትከል፣ ቆሻሻን ባገኘነው ቦታ ሁሉ አለመጣል እና የዱር እንስሳትን መንከባከብ። አካባቢያችንን ለመንከባከብ የምንችለውን ሁሉ ማድረግ አለብን። የኦሮሞ ህዝብ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ፍልስፍና እና ህጎች አሉት። በዚህም መሰረት "መጀመሪያ ከራስህ ጋር ታረቅ፣ ከዚያም ከጎረቤትህ ጋር ታረቅ ከዚያም አካባቢህን በመንከባከብ ሰላም ሁን" ይላል። በዚህ ረገድ የኦሮሞ ህዝብ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ከሚቀበላቸው የግብረገባዊነት ደንቦች ጥቂቶቹ፡-

- ታዳጊ ዛፎች አይቆረጡም፡፡
- እንስሳትን ካጠጣ በኋላ ገንዳውን ለዱር እንስሳት እንዲሆን ውኃ መሙላት፡፡
- ቁጥራቸው የተመናነመኑ የዱር እንስሳትን በሰው ስም በመሰየም መንከባከብ።

አካባቢያችንን አረንጓዴ ለማድረግ ብዙ መንገዶች አሉ። የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ ከተንከባከብን ለመጪው ትውልድ የተሻለ አካባቢን እናወርሳለን።

ስለዚህ የተፈጥሮን ሥነ ምህዳር ለመጠበቅ አካባቢያችንን መንከባከብ የሁላችንም ግዴታ ነው።

### 4.2.3 የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳርያ**

ገበታዎች፣ ፎቶዎች፣ ቪዲዮዎች፣ ፊልሞች፣ መጣጥፎች፣ ብሮሹሮች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ግራፎች፣ ፖስተሮች፣ ፎቶግራፍ፣ ግራፎች፣ ካርታዎች፣ ምሳሌዎች፣ መጽሔቶች እና ጋዜጦች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

የቡድን ውይይት፣ ክርክር፣ ሚና መጫወት፣ ድራማ፣ ጥያቄ እና መልስ

**ቅድመ ትምህርት  ዝግጅት**

መምህር፤ በኢትዮጵያ እና በሌሎችም አካባቢዎች የአካባቢ ጥበቃን አስፈላጊነት የሚያሳዩ የትምህርት እቅዶችን እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ።

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

ያለፈውን ትምህርት በአጭሩ ከልሰው የእለቱን ትምህርት ርዕስ 'የአካባቢ እንክብካቤ ምንንት'ን ያስተዋውቁ። የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት ከአዲሱ ትምህርት ጋር በማዛመድ የተማሪዎችን ፍላጎት ያነሳሱ። በተጨማሪም ስዕሎችን፣ ገበታዎችን እና ሞዴሎችን ማሳየት ይችላሉ። ይህም ተማሪዎች ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር እና ትምህርቱ ተጨባጭ እንዲሆን ይረዳል።

**ለ. አቀራረብ**

መምህር፤ በዚህ ክፍል ለተማሪዎችዎ የትምህርቱን አላማ ይግለጹላቸው፤ እንዲሁም ከአዳዲስ መረጃዎች ጋር አስተዋውቋቸው፣ ከዚያም የእለቱን ትምህርት ያቅርቡላቸው። ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ፣ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም፣ ትምህርቱን መረዳታቸውን

የሚገመግሙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ከተማሪዎች ግብረ መልስ ማግኘት መቻል አለብዎት።

### ሐ. ማጠናከሪያ

መምህር፤ የእርስዎ ዋና ተግባር ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማገዝ ይሆናል። ለዚህም የእለቱን ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦች በጥያቄ መልክ አቅርቡላቸው። የተማሪዎች ምላሽ ያልተሟላ ወይም የተሳሳቱ ከሆኑ ያርሙዋቸው።

## 4.2.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ። ምሳሌ፡ አካባቢን መንከባከብ ምን ጥቅሞች አሉት?

### ለ. ክትትል

ተማሪዎችን አዳዲስ ፅንሰሀሳቦችን እና ክህሎቶችን ሲተገብሩ የተማሪዎችን ዕውቀት እና ክህሎቶች ይከታተሉ። ተማሪዎች አስተሳሰባቸውን ወይም ባህሪያቸውን እንደለወጡ የሚያሳይ ማስረጃ ይፈልጉ። በተጨማሪም በቡድን የላቸውን ተሳትፎ ይከታተሉ።

## 4.2.5. የትምህርት 2 ተግባራት መልስ

### ተግባር 2

1. የአካባቢ እንክብካቤ አካባቢያችንን ለኑሮ ምቹ ለማድረግ የምናደርጋቸውን ተግባራት ሁሉ ያጠቃልላል። ለምሳሌ ችግኞችን መትከል፣ ቆሻሻን ባገኘንበት ቦታ ሁሉ አለመጣል እና የዱር እንስሳትን መንከባከብ።

2. ስለ አካባቢ ጥበቃ የኦሮሞ ፍልስፍና

ሀ. ታዳጊ  ችግኞችን አይቆርጡ/ተንከባከቡ

ለ. የውሃ ምንጭ ንፅህና መጠበቅ/ የውሃ ሀብትን መንከባከብ

## 4.3. ትምህርት 3፡ የአካባቢ እንክብካቤ አስፈላጊነት

**የክፍለ ጊዜ መጠን 5**

### 4.3.1. ይዘት

- የአካባቢ እንክብካቤ አስፈላጊነት

### 4.3.2 አጠቃላይ መግለጫ

አካባቢያችን የምንኖርበት ብቻ ሳይሆን ለህልውና ወሳኝ ቦታ ነው፡፡ የምንበላው፣ የምንጠጣው፣ የምንለብሰው፣ የምንተነፍሰው አየር እና የምንኖርበት ቤት ከአካባቢው የሚገኙ ናቸው። ስለዚህ ለአካባቢ እንክብካቤ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በአካባቢ ላይ የምናደርጋቸው ድርጊቶች ሰዎች እና በአካባቢው ያሉ ነገሮችን ችግር ውስጥ ሊጥሉ ይችላሉ። ስለዚህ ከአካባቢ ጋር የምንገናኝበት መንገድ በአካባቢ ላይ ተጽእኖ የማያሳድር መሆን አለበት፤ ተግባራችን አካባቢን ሊጎዳ ይችላል ወይ ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ እና ማስተካከል አለብን፤ በአጠቃላይ አካባቢን መንከባከብ የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት።

- የመኖሪያ ቦታችንን ምቹ ለማድረግ
- ንጹህ አካባቢ ለመፍጠር
- የሙቀት መጨመርን ለመቆጣጠር
- የአካባቢን ስነምህዳር ሚዛን ለመጠበቅ
- የመኖሪያ ቦታዎችን ለመጠበቅ
- አስፈላጊ የሆኑ የምግብ ምንጮችን ለመጠበቅ
- አካባቢን የመንከባከብ የሞራል ግዴታ ስላለብን ነው።

### 4.3.3. የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

ገበታዎች፣ ፎቶዎች፣ ቪዲዮዎች፣ ፊልሞች፣ መጣጥፎች፣ ብሮሹሮች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ግራፎች፣ ፖስተሮች። የፎቶግራፍ ግራፎች፣ ካርታዎች፣ ምሳሌዎች፣ መጽሔቶች እና ጋዜጦች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

የቡድን ውይይት፣ ክርክር፣ ሚና መጫወት፣ ድራማ፣ ጥያቄ እና መልስ

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

በኢትዮጵያ እና በሌሎችም አካባቢዎች የአካባቢ ጥበቃን አስፈላጊነት የሚያሳዩ የትምህርት እቅዶችን እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ።

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

ያለፈውን ትምህርት በአጭሩ ከልሰው የእለቱን ትምህርት ርእስ "የአካባቢ እንክብካቤ አስፈላጊነት'ን ያስተዋውቁ። የተማሪውን የቀደመ እውቀት እና አዲሱን ትምህርት በማዛመድ የተማሪዎችን ፍላጎት ከፍ ያድርጉ። ይህም የተማሪዎችን ተነሳሽነት በማሳደግ ለትምህርቱ እንዲዘጋጁ ይረዳል። በተጨማሪም ስዕሎችን፣ ገበታዎችን፣ ሞዴሎችን እና ታሪኮችን ማሳየት ይችላሉ።

**ለ. አቀራረብ**

መምህር፤ በዚህ ክፍል ለተማሪዎችዎ የትምህርቱን አላማ ይግለጹላቸው፤ እንዲሁም ከአዳዲስ መረጃዎች ጋር አስተዋውቋቸው፣ ከዚያም የእለቱን ትምህርት ያቅርቡላቸው። ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ፣ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም፣ ትምህርቱን መረዳታቸውን የሚገመግሙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ከተማሪዎች ግብረ መልስ ማግኘት መቻል አለብዎት።

**ሐ. ማጠናከሪያ**

መምህር፤ የእርስዎ ዋና ተግባር ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማገዝ ይሆናል። ለዚህም የእለቱን ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦች በጥያቄ መልክ አቅርቡላቸው። የተማሪዎች ምላሽ ያልተሟላ ወይም የተሳሳቱ ከሆኑ ያርሙዋቸው።

### 4.3.4. ምዘና እና ክትትል

**ሀ. ምዘና**

የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ።ለምሳሌ አካባቢን መንከባከብ ምን ጥቅሞች አሉት?

**ለ. ክትትል**

ተማሪዎችን አዳዲስ ፅንሰሀሳቦችን እና ክህሎቶችን ሲተገብሩ የተማሪዎችን ዕውቀት እና ክህሎቶች ይከታተሉ። ተማሪዎች አስተሳሰባቸውን ወይም ባህሪያቸውን እንደለወጡ የሚያሳይ ማስረጃ ይፈልጉ። በተጨማሪም በቡድን የላቸውን ተሳትፎ ይከታተሉ።

### 4.3.5. የትምህርት 3 ተግባራት መልስ

**ተግባር 3**

1. ሰዎችም ሆኑ እንስሳት ያለ አካባቢ መኖር ስለማይችሉ
2. ሀ. አካባቢያችንን ለኑሮ ምቹ ለማድረግ፤
   ለ. የፍጥረታትን ንጥረምግቦችን እና መድሃኒቶችን ለመጠበቅ፤
   ሐ) ሕይወት ያላቸውን ነገሮች ከመጥፋት ለመጠበቅ፤

# 4.4. ትምህርት 4፡ አካባቢን የመንከባከብ መንገዶች

**የክፍለ ጊዜ መጠን 5**

## 4.4.1 ይዘቶች

- አካባቢን የመጠበቅያ መንገዶች

## 4.4.2 አጠቃላይ መግለጫ

በአካባቢያችን ቀላል ናቸው ብለን የምናስባቸው ነገሮች በሂደት ከፍተኛ ብክነትን ሊያስከትሉ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ከውሃ ጋር በተያያዘ ከተጠቀምን በኋላ ቧንቧውን መዝጋት ውሃ እንዳናባክን ያደርገናል፣ እንዲሁም የሚያንጠባጥብ ቧንቧ ካለን ቶሎ ማስተካከል አስፈላጊ ነው።

**የመማር ማስተማር ሂደት**

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ገበታዎች፣ ፎቶዎች፣ ቪዲዮዎች፣ ፊልሞች፣ መጣጥፎች፣ ብሮሸሮች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ግራፎች፣ ፖስተሮች። የፎቶግራፍ ግራፎች፣ ካርታዎች፣ ምሳሌዎች፣ መጽሔቶች እና ጋዜጦች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

የቡድን ውይይት፣ ክርክር፣ ሚና መጫወት፣ ድራማ፣ ጥያቄ እና መልስ

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

በኢትዮጵያ እና በሌሎችም አካባቢዎች የአካባቢ ጥበቃን አስፈላጊነት የሚያሳዩ የትምህርት እቅዶችን እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ።

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

ያለፈውን ትምህርት በአጭሩ ከልሰው የእለቱን ትምህርት ርእስ "አካባቢን የመንከባከቢያ መንገዶች'ን ያስተዋውቁ። የተማሪውን የቀደመ እውቀት እና አዲሱን ትምህርት በማዛመድ የተማሪዎችን ፍላጎት ከፍ ያድርጉ። ይህም የተማሪዎችን ተነሳሽነት በማሳደግ ለትምህርቱ እንዲዘጋጁ ይረዳል።

በተጨማሪም ስዕሎችን፣ ገበታዎችን፣ ሞዴሎችን እና ታሪኮችን ማሳየት ይችላሉ።

**ለ. አቀራረብ**

መምህር፤ በዚህ ክፍል ለተማሪዎችዎ የትምህርቱን አላማ ይግለጹላቸው፤ እንዲሁም ከአዳዲስ መረጃዎች ጋር አስተዋውቋቸው፣ ከዚያም የእለቱን ትምህርት ያቅርቡላቸው። ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ፣ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም፣ ትምህርቱን መረዳታቸውን የሚገመግሙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ከተማሪዎች ግብረ መልስ ማግኘት መቻል አለብዎት።

**ሐ. ማጠናከሪያ**

መምህር፤ የእርስዎ ዋና ተግባር ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማገዝ ይሆናል። ለዚህም የእለቱን ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦች በጥያቄ መልክ አቅርቡላቸው። የተማሪዎች ምላሽ ያልተሟላ ወይም የተሳሳቱ ከሆኑ ያርሙዋቸው።

### 3.4.4. ምዘና እና ክትትል

**ሀ. ምዘና**

የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ። ለምሳሌ፣ አካባቢን የመጠበቂያ መንገዶች ምንድናቸው?

**ለ. ክትትል**

ተማሪዎችን አዳዲስ ፅንሰሀሳቦችን እና ክህሎቶችን ሲተገብሩ የተማሪዎችን ዕውቀት እና ክህሎቶች ይከታተሉ። ተማሪዎች አስተሳሰባቸውን ወይም ባህሪያቸውን እንደለወጡ የሚያሳይ ማስረጃ ይፈልጉ። በተጨማሪም በቡድን የላቸውን ተሳትፎ ይከታተሉ።

### 3.4.5. የትምህርት 4 ተግባራት መልስ

**ተግባር 4**

1. አካባቢን የመጠበቅ ዘዴዎች፡-

ሀ. ቆሻሻን መቆጣጠር

ለ. ውሃ መጠበቅ

ሐ. ለአካባቢ ተስማሚ የኃይል ምንጮችን መጠቀም

መ. አካባቢን የሚበክሉ ኬሚካሎችን መቀነስ

2. የውሀ ጥበቃ አስፈላጊነት

ሀ. ሰው ያለ ውሃ መኖር ስለማይችል

ለ. ምክንያቱም ውሃ የፍጥረታት ሁሉ መሠረት ስለሆነ

## 4.5. ትምህርት 5፡ ለአካባቢ እንክብካቤ አለመስጠት የሚያስከትለው ጉዳት

**የክፍለ ጊዜ መጠን 3**

### 4.5.1. ይዘት

- የውሃ እጥረት
- የአየር መበከል
- የምግብ እጥረት
- ህይወት ያላቸው ዝርያዎች መጥፋት

### 4.5.2 አጠቃላይ መግለጫ

አካባቢ ለመኖር የሚያስፈልጉን ነገሮች ሁሉ አሉት፤ ነገር ግን የምንፈልገውን ሁሉ እንዲሰጠን ያለማቋረጥ መንከባከብ አለብን። አካባቢን መንከባከብ ማለት ምድርን የማይረብሽ ወይም የማይበክሉ ነገሮችን ማድረግያስፈልጋል፡፡ አካባቢን ለመጠበቅ የምንችለውን ሁሉ ማድረግ የኛ ፈንታ ነው። አካባቢያችንን እና ፕላኔታችንን አረንጓዴ ለማድረግ ብዙ አማራጮች አሉን። አካባቢን ካልተንከባከብን የውሃ እጥረት፣ የአየር ብክለት፣ የምግብ እጥረት፣ የተለያዩ ዝርያዎች መጥፋት ይገጥመናል።

**የመማር ማስተማር ሂደት**

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ገበታዎች፣ ፎቶዎች፣ ቪዲዮዎች፣ ፊልሞች፣ መጣጥፎች፣ ብሮሸሮች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ግራፎች፣ ፖስተሮች። የፎቶግራፍ ግራፎች፣ ካርታዎች፣ ምሳሌዎች፣ መጽሔቶች እና ጋዜጦች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

የቡድን ውይይት፣ ክርክር፣ ሚና መጫወት፣ ድራማ፣ ጥያቄዎች እና መልሶች

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

በኢትዮጵያ እና በሌሎችም አካባቢዎች የአካባቢ ጥበቃን አስፈላጊነት የሚያሳዩ የትምህርት እቅዶችን እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ።

## የትምህርቱ አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

ያለፈውን ትምህርት በአጭሩ ከልሰው የእለቱን ትምህርት **'ለአካባቢ እንክብካቤ አለመስጠት የሚያስከትለው ጉዳት'** ርእስን ያስተዋውቁ። የተማሪውን የቀደመ እውቀት እና አዲሱን ትምህርት በማዛመድ የተማሪዎችን ፍላጎት ከፍ ያድርጉ። ይህም የተማሪዎችን ተነሳሽነት በማሳደግ ለትምህርቱ እንዲዘጋጁ ይረዳል። በተጨማሪም ስዕሎችን፣ ገበታዎችን፣ ሞዴሎችን እና ታሪኮችን ማሳየት ይችላሉ።

### ለ. አቀራረብ

መምህር፤ በዚህ ክፍል ለተማሪዎችዎ የትምህርቱን አላማ ይግለጹላቸው፤ እንዲሁም ከአዳዲስ መረጃዎች ጋር አስተዋውቋቸው፣ ከዚያም የእለቱን ትምህርት ያቅርቡላቸው። ትምህርቱን ውጤታማ ለማድረግ፣ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም፣ ትምህርቱን መረዳታቸውን የሚገመግሙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ከተማሪዎች ግብረ መልስ ማግኘት መቻል አለብዎት።

### ሐ. ማጠናከሪያ

መምህር፤ የእርስዎ ዋና ተግባር ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማገዝ ይሆናል። ለዚህም የእለቱን ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦች በጥያቄ መልክ አቅርቡላቸው። የተማሪዎች ምላሽ ያልተሟላ ወይም የተሳሳቱ ከሆኑ ያርሙዋቸው።

## 4.5.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ።

### ለ. ክትትል

ተማሪዎችን አዳዲስ ፅንሰሀሳቦችን እና ክህሎቶችን ሲተገብሩ የተማሪዎችን ዕውቀት እና ክህሎቶች ይከታተሉ። ተማሪዎች አስተሳሰባቸውን ወይም

ባህሪያቸውን እንደለወጡ የሚያሳይ ማስረጃ ይፈልጉ። በተጨማሪም በቡድን የላቸውን ተሳትፎ ይከታተሉ።

### 4.5.5 የትምህርት 5 ተግባራት መልስ

**ተግባር 5**

1. ለአካባቢ ጥበቃ ያለማድረግ ከሚያደርሱት ጉዳቶች መካከል፡-

ሀ. የውሃ እጥረት	ለ. የአየር ብክለት

ሐ. የምግብ እጥረት

መ. ህይወት ያላቸው ዝርያዎች መጥፋት

2. ሁሉም ህይወት ያላቸው ነገሮች

## 4.6. የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

**ትእዛዝ I: እውነት ወይም ሀሰት**

1. እውነት	2. ሀሰት

ትዕዛዝ II: ትክክለኛውን መልስ ይምረጡ

1. መ	2. ሐ	3. ለ	4. መ

**ትዕዛዝ III፡ አጭር መልስ**

**ጥያቄ** 1፡- አካባቢን የመጠበቂያ መንገዶች ጥቂቶቹ፡-

ሀ. ቆሻሻን መቆጣጠር	ለ. የውሃ ጥበቃ

ሐ. ለአካባቢ ተስማሚ የኃይል ምንጮችን መጠቀም

መ. አካባቢን የሚበክሉ ኬሚካሎችን መቀነስ

**ጥያቄ** 2፡- አካባቢን ባለመንከባከብ ምክንያት ከሚደርሱ ጉዳቶች መካከል ጥቂቶቹ

1. የውሃ እጥረት	2. የአየር ብክለት

3. የምግብ እጥረት

4. ህይወት ያላቸው ዝርያዎች መጥፋት

# ምዕራፍ 5 የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር

## መግቢያ

ተማሪዎች ከማህበራዊ ሚዲያ መማር ሲጀምሩ ተሳትፏቸው እየጨመረ ይሄዳል፡፡ አስቀድሞ ግን የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም መመሪያዎችን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከትምህርት ዋነኛ አላማዎች አንዱ ራስን እና ህብረተሰብን ማገልገል ነው። ህብረተሰብን ለማገልገል ደግሞ በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍ ያለ ተቀባይነት ያላቸውን እሴቶች መጠበቅና ተንከባክቦ ለቀጣዩ ትውልድ ማስተላለፍ ይገባል። ስለሆነም ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ተግባቦት በምናከናውንበት ወቅት እነዚህን እሴቶችና ሌሎች የአጠቃቀም ህጎችን ተከትለን መሆን ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ ግን በራስም ሆነ በሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች ሊከተል የሚችለው ጉዳት ሊገመት የማይችል ይሆናል።

ይህ ምዕራፍ በአራት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ትምህርትም የየራሱ ይዘት አለው። የመጀመሪያው ክፍል ስለማህበራዊ ሚዲያ ምንነት፣ ሁለተኛው ደግሞ ስላስፈላጊነቱ፣ ሦስተኛው ክፍል ስለአጠቃቀም ስነምግባር እና አራተኛውና የመጨረሻ ክፍል ደግሞ ማህበራዊ ሚዲያን አለአግባብ መጠቀም ስለሚያስከትላቸው ጉዳቶች የሚያትት ነው።

እነዚህን የትምህርት ይዘቶች ከግቡ ለማድረስ ዋና ዋናዎቹ የመማር እና የማስተማር ዘዴዎች የቡድን ውይይቶች፣ ማብራሪያዎች፣ ምስሎች፣ ትረካዎች፣ ማሳያዎች፣ ጉብኝቶች፣ ጥያቄና መልሶች እና ገለጻዎች ናቸው።

ተማሪዎችን የሚያነቃቁ አንዳንድ ጥያቄዎች እና ተግባራትም በምዕራፍ ትምህርቱ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርገዋል። በመጨረሻም የምዕራፉን መልእክት የሚቋጭ ማጠቃለያ እና መለማመጃዎች ቀርበውበታል።

**የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፡-**

- ማህበራዊ ሚዲያ ማለት ምን ማለት እንደሆነ መረዳት፣
- የማህበራዊ ሚዲያ አይነቶችን መዘርዘር፣

- የማህበራዊ ሚዲያን አስፈላጊነት ማስረዳት፣
- የማህበራዊ ሚዲያ ስነምግባርን ማሳየት፣
- የማህበራዊ ሚዲያን አላግባብ መጠቀም የሚያስከትለውን ጉዳት መለየት።

**ለምዕራፉ የተመደቡ ጠቅላላ ክፍለ ጊዜ፡- 18**

**የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ይዘቶች**

ትምህርት 1፡ የማህበራዊ ሚዲያ ተፈጥሮ

ትምህርት 2፡ የማህበራዊ ሚዲያ አስፈላጊነት

ትምህርት 3፡ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር

ትምህርት 4 የማህበራዊ ሚዲያ አለአግባብ መጠቀም ጉዳቱ

## 5.1. ትምህርት 1፡ የማህበራዊ ሚዲያ ምንነት

**ለዚህ ርዕስ የተመደበው ጠቅላላ ክፍለጊዜ 3**

### 5.1.1. ይዘት

ማህበራዊ ሚዲያ

### 5.1.2. አጠቃላይ መግለጫ

ማህበራዊ ሚዲያ የመገናኛ ሞዛይክ (ድረ-ገጽ) እና የመስመር ላይ እንደ ፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ኢንስታግራም፣ ቴሌግራም፣ ዩቲዩብ፣ ሊንክድን፣ ትሬድ የመሳሰሉትን ያካትታል። በርካታ ማህበረሰቦች መረጃን ለመለዋወጥ፣ ሙያዊና ማህበራዊ ደረጃን ለማጎልበት እና ንግድን ለማስፋፋት ይጠቀሙባቸዋል። ወደ ትምህርቱ አለም ስንመጣም ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ተማሪዎች ማህበራዊ መገናኛዎችን በአግባቡ በመጠቀም እውቀትና ክህሎታቸውን እጅጉን እያሻሻሉባቸው ይገኛሉ። ማህበራዊ መገናኛዎቹ ተጨማሪ ገለጻዎችንና ምሳሌዎችን በቀላሉ ተደራሽ ስለሚያደርጉ ክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ይበልጥ ተጨባጭ ያደርጉታል። ይህም ተማሪዎቹ በትምህርት ተቋሞቻቸው የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ይረዳቸዋል። ይሁን እንጂ በማህበራዊ መገናኛዎች የሚቀርቡት መረጃዎች ሁሉም ትክክለኛና ጠቃሚ ናቸው ተብሎ

አይታሰብም። ስለሆነም በአጠቃቀም ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። ለዚህም የወላጆችና የመምህራን ክትትልና እገዛ በጣም አስፈላጊ ይሆናል።

### 5.1.3. መማር ማስተማር ሂደት

### የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

ገበታዎች፣ የቪዲዮ ቴፕ ምስሎች፣ በራሪ ጽሑፎች፣ ፊልሞች፣ ብሮሸሮች፣ ግራፎች፣ ካርታዎች፣ ሥዕሎች፣ ካርቱን

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

እባክዎ መምህር ተማሪዎችዎ ስለማህበራዊ መገናኛዎች ያላቸውን ግንዛቤ ለማወቅ ይረዳ ዘንድ ስለምንነቱ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። በተጨማሪም ምስል 5.1 ን እንዲመለከቱና ስለምስሉ ምን እንደሚያስቡ ይጠይቁ።

አነስተኛ የአባላት ቁጥር ባላቸው ቡድኖች በማደራጀትም በተግባር 1 እና 2 ላይ እንዲወያዩና የደረሱበትን ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ያበረታቱ። ትኩረታቸውን ይዞ ለመቀጠልም ከማህበራዊ መገናኛዎች ምንነት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው፤ እየተዘዋወሩም ምልከታ ያድርጉ።

### የትምህርት ቅድመ ዝግጅት

ውድ መምህር ለተማሪዎችዎ ስለማህበራዊ ሚዲያ /መገናኛዎች/ ገለጻ ከማቅረብዎ በፊት ለራስዎ በቂ ዝግጅት ያድርጉ። ለዚህም የተለያዩ መረጃ ምንጮችን ይመልከቱ፤ የተገኙ መረጃዎችም የተማሪዎቹን ልምድና የክፍል ደረጃ በሚመጥን መልኩ አደራጅተው ይጠቀሙባቸው።

### የትምህርቱ አቀራረብ

**ሀ. መግቢያ፡**

ተማሪዎቹን የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን ይጀምሩ።

- ➢ ከስእል 5.1 ምን ተረዳችሁ?
- ➢ የማህበራዊ ሚዲያን ምንነት ታውቃላችሁ? (ማህበራዊ ሚዲያ ምንድን ነው?)

## ለ. አቀራረብ

የማህበራዊ ሚዲያ ምንነትን መግለጽ፤

ማህበራዊ መገናኛ ብዙኃንን በተመለከተ በተማሪ መጽሐፍ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ አሳታፊ ገለጻ ያድርጉ። ዋና ዋና ነጥቦችንም ሰሌዳ ላይ ያስፍሩ።

## ሐ. ማጠናከሪያ

ተማሪዎች በዕለቱ የተማሩትን በትክክል እንዲያብራሩ ዕድል ይስጧቸው፤ የዕለቱን ትምህርት አበይት ነጥቦች መልሰው እንዲናገሩ ያበረታቷቸው። ማጠቃለያ ይስጡ።

## 5.1.4. ምዘና እና ክትትል

## ሀ. ምዘና

የዕለቱ ትምህርት ግብ መሳካት አለመሳካቱን ለማረጋጥና የተማሪዎችን ግንዛቤ ለማጠናከር በክፍል ጊዜው ማጠናቀቂያ ላይ ሁልጊዜ ምዘና ማካሄድ ይገባል። ምዘና ሲካሄድ የተለያዩ መነገዶችን መከተል የሚቻል ሲሆን ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲረዱት የክፍል ስራ በመስጠት፣ የቡድን ስራዎችን በማሰራት ወይም ተማሪዎችን በቡድን በማደራጀት እንዲወያዩ በማበረታታት ወዘተ መገምገም ይቻላል። ለምሳሌ ከሥዕሉ ምን እንደተረዱ ሀሳብ እንዲጡ ይጠይቋቸው፡፡

## ለ. ክትትል፡

- ተማሪዎች የማህበራዊ ሚዲያን ምንነት እንዲገልጹ ማበረታታት፤
- ተማሪዎች የቡድን ውይይት ሃሳባቸውን እንዲገልጹ መርዳት፤
- እየተዘዋወሩ ተሳትፎ እያደረጉ ስለመሆኑ መመልከት።

### 5.1.5. የትምህርት 1 ተግባራት መልስ

**ተግባር 1**

1. ማህበራዊ ሚዲያ በኢንተርኔት መረብ አማካኝነት ሰዎች ፊትለፊት በአካል ሳይገናኙ ወይም ጊዜና ቦታ ሳይወስናቸው በቴክኖሎጂ ውጤቶች ተግባቦትን የሚያካሂዱበት ነው።

2. ማህበራዊ ሚድያ የሚባሉት፡-

   ሀ) ፌስቡክ

   ለ) ቴሌግራም

   ሐ) ዩቲውብ

   መ) ኢንስታግራም

   ሠ) ትዊተርና የመሳሰሉት ናቸው

## 5.2. ትምህርት 2፡ የማህበራዊ ሚዲያ ጠቀሜታ

**የክፍለ ጊዜ መጠን 3**

### 5.2.1. ይዘት፡-

የማህበራዊ ሚዲያ ጠቀሜታ

### 5.2.2. አጠቃላይ መግለጫ

ማህበራዊ ሚዲያ ተማሪዎች በመስመር ላይ በቀላሉ እንዲግባቡ አድርጓል። ስለዚህ፣ ማህበራዊ ሚዲያ ለተማሪዎች ከሚፈጥራቸው እድሎች መካከል፡-

- በማንኛውም የአለም ጥግ ላይ ያሉ ክስተቶችን በቅጽበት እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል።
- በኦን-ላይን እርስ በርስ እንዲተዋወቁ እና ጓደኞች እንዲያፈሩ ይረዳቸዋል።
- ተጨማሪ መረጃን በእጃችን ይሰጠናል።
- መማር ለሚፈልጓቸው ጉዳዮች ትክክለኛዎቹን የማስረጃ ምንጮች እንዲመርጡ ይረዳቸዋል።

## 5.2.3. ለመማር የማስተማር ሂደት

### የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ተንሸራታች ገበታዎች፣ የቪዲዮ ምስሎች፣ ካሴቶች፣ ፓምፕሌቶች፣ ፊልሞች፣ ብሮሸሮች፣ ግራፊክስ፣ ካርታዎች፣ ሥዕሎች፣ ካርቶኖች

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ማህበራዊ ሚዲያ በትምህርታቸው፣ በእኩዮቻቸው እና በማህበረሰቡ መካከል ስላለው ግንኙነት የተማሪዎችን ግንዛቤ ጥያቄዎችን ይጠይቁ።

ትምህርቱን ከማቅረብዎ በፊት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አለብዎት፤ ተማሪዎችን ስለማህበራዊ ሚዲያ አስፈላጊነት ለማስተማር እራስዎን በአግባቡ ያዘጋጁ፡፡

### የትምህርቱ አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን ይጀምሩ።

- ማህበራዊ ሚዲያ ለተማሪዎች ጠቃሚ ነው?እንዴት?

### ለ. አቀራረብ

የማህበራዊ ሚዲያ ጠቀሜታ

- በግለሰብ ደረጃ
- በሙያ ደረጃ
- በተቋም ደረጃ (እነዚህን ጉዳዮች በትክክል ያብራሩ)

### ሐ. ማጠናከሪያ

ተማሪዎች ዛሬ የተማሩትን በትክክል እንዲያብራሩ ያድርጉ እና የዛሬውን ትምህርት ዋና ዋና ነጥቦች እያነሱ ማብራሪያ ይስጡ።

## 5.2.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

የቀረበውን ትምህርት ለማጠናከር ሁልጊዜ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ምዘና ያካሂዱ።

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት እንዲረዱት የክፍል ስራዎችን በመስጠት፣ የቡድን ስራዎችን በማሰራት ወይም የማህበራዊ ሚዲያ አስፈላጊነት ላይ እንዲወያዩ በማበረታታት ወዲያውኑ መገምገም ይችላሉ።

የማህበራዊ ሚዲያ ጥቅሞችን በግል፣ በሙያዊ እና በድርጅት ደረጃ እንዲገልጹ ጠይቃቸው።

**ለ. ክትትል፡**

ተማሪዎች ስለ ማህበራዊ ሚዲያ አስፈላጊነት እንዲወያዩ አበረታቷቸው፡ ተማሪዎች የቡድን ውይይት ሃሳባቸውን እንዲገልጹ እርዷቸው። እየተዘዋወሩ ይቃኙአቸው፣ እርማት የሚሰጥባቸው ስራዎች ካሉ ደብተሮቻቸውን ሰብስበው አወንታዊ ምጋቤ ምላሽ ይስጧቸው።

### 5.2.5. የትምህርት 2 ተግባራት መልስ
### ተግባር 2

- ❖ ማህበራዊ ሚዲያ በስነምግባር ከተጠቀምንበት የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት፡፡

1. ከብዙ ሰዎች ጋር በአንድ ጊዜ ለመገናኘት እና መረጃን ለመጋራት ያስችላል።
2. ወቅታዊ መረጃን ለማግኘት ይረዳል።
3. በማንኛውም የአለም ጥግ ላይ ያሉ ክስተቶችን በቅጽበት እንድናውቅ ያደርገናል።
4. ስለአለም ያለንን ምልከታ (ርዕዮት) ያሰፋል ወዘተ።

## 5.3. ትምህርት 3፡ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር

**የክፍለ ጊዜ መጠን 5**

### 5.3.1. ይዘት

- የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር

### 5.3.2. አጠቃላይ መግለጫ

ተማሪዎች የመዝናኛ ማህበራዊ ሚዲያዎችን ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ክህሎት እና ስነምግባር ማዳበር አለባቸው፤ ይህ ምንም ጉዳት በሌለው መንገድ መከናወን አለበት። ወላጆቻቸው በሌሉበት ማህበራዊ ሚዲያዎችን ሲጠቀሙ ለቤተሰቦቻቸው ታማኝ መሆን አለባቸው። በሚዲያ አጠቃቀም ላይ ያላቸውን አቋም ለቤተሰቦቻቸው ማሳወቅ አለባቸው፡፡

### 5.3.3 የመማር እና የማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

የተንሸራታች ሥዕሎች፣ ምስሎች፣ በራሪ ጽሑፎች፣ ፊልሞች፣ ብሮሸሮች፣ ግራፎች፣ ካርታዎች፣ ሥዕሎች፣ ካርቶኖች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

ስለ ማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር የተማሪዎችን ግንዛቤ ለመፈተሽ ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡፡ ከቤተሰብ እና መምህራን ጥምረት አባላት መካከል የተወሰኑ ግለሰቦችን በመጋበዝ ስለማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር ለክፍሉ እንዲያብራሩ ያድርጉ። ተማሪዎችም ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው።

አነስተኛ የአባላት ቁጥር ያላቸው ቡድኖችን ይፍጠሩ እና በማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር ዙሪያ ተማሪዎች እንዲወያዩና ሀሳባቸውን ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ያድርጓቸው።

ተማሪዎችዎን ስለማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር ለማስተማር ከመጀመርዎ በፊት ግን አስቀድመው እራስዎን በአግባቡ ያዘጋጁ።

## የትምህርቱ አቀራረብ

**ሀ. መግቢያ፡**

- ማህበራዊ ሚዲያ ስንጠቀም ልንከተላቸው የሚገቡን ስነምግባሮች ምን ምን ናቸው?
- ማህበራዊ ሚዲያን ስንጠቀም የአጠቃቀም ስነምግባሮችን የማንከተል ከሆነ ምን ችግር የሚያጋጥመን ይመስላችኋል? የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማስተማር ይጀምሩ።

**ለ. አቀራረብ**

- የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባርን ያብራሩ፡፡
- ማህበራዊ አውታረ መረቦችን ሲጠቀሙ ምን ማድረግና ምን ማድረግ እንደሌለብዎት ያብራሩ፡፡

**ሐ. ማጠናከሪያ**

ተማሪዎች በዕለቱ የተማሩትን ትምህርት እያስታወሱ መልሰው እንዲናገሩ ያድርጉ። በመጨረሻም እርስዎ የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች ይከልሱላቸው።

### 5.3.4. ምዘና እና ክትትል

**ሀ. ምዘና**

የሚጠበቀው ውጤት መምጣቱን ለማረጋገጥ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ሁልጊዜም ምዘና ያካሂዱ። ተማሪዎች ይህንን ትምህርት እንዲረዱት ወዲያውኑ የቡድን ስራዎችን በመስጠት፣ በቡድን በማደራጀት እና በተለያዩ የማህበራዊ ሚዲያ ስነምግባሮች ላይ እንዲወያዩ በማበረታታት የክፍል ስራውን መገምገም ይችላሉ።

ጥያቄ፡- ሀ) የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነ ምግባር ምንድን ነው?

ለ) ማህበራዊ ሚዲያን ስንጠቀም መከተል ያሉብን ስነምግባሮች ምን ምን ናቸው?

## ለ. ክትትል

ተማሪዎች ስለ ማህበራዊ ሚዲያ አስፈላጊነት እንዲወያዩ ያበረታቷቸው። ተማሪዎች በማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር ላይ እንዲወያዩ እና የቡድን ውይይት ሃሳቦቻቸውን ለክፍል እንዲያሳውቁ ለመርዳት ትንንሽ ቡድኖችን በማዋቀር ክትትል ያድርጉ።

## 5.3.5.የትምህርት ሶስት ተግባራት መልስ

### ተግባር 3

❖ የማህበራዊ ሚዲያ ስንጠቀም መከተል ያለብን የስነምግባር መመሪያዎች

1. መልዕክት ስንለዋወጥ የአክብሮት ቃላትን መጠቀም፤
2. የምንቀበላቸውን መልዕክቶች ሳናረጋግጥ ለሌሎች አለማካፈል፤
3. የህዝብን ስነ ምግባር የሚጥስ መረጃ ከመስጠት እና ከመቀበል መቆጠብ፤
4. ያለፈቃድ የአንድን ሰው ፎቶ ወይም ቪዲዮ አለመለጠፍ፤
5. ማህበራዊ ሚዲያን ለአዎንታዊ ነገሮች ብቻ መጠቀም፤
6. የሐሰት መረጃን አለማሰራጨት፤
7. በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ብዙ ጊዜ ከማሳለፍ መቆጠብ፤
8. የማህበረሰባችንን እሴቶች መጠበቅ (አለመዋሸት፣ አለመስደብ፣ ስም አለማጥፋት)

❖ የኦሮሞ ህዝብ እሴቶች

1. ሀቀኝነት 2. ሀሰት መጠየፍ 3. መከባበር

# 5.4. ትምህርት 4፡ ማህበራዊ ሚዲያን አላግባብ የመጠቀም ጉዳቶች

**የክፍለ ጊዜ መጠን 7**

## 5.4.1. ይዘቶች

- በማህበራዊ ሚድያ መጠቀም ሱስ መጠመድ
- ስድብ (ዛቻ)
- የሞራል መሰበር፣ የስሜት መጎዳት
- ማግለል(መፎገር)
- መሳለቅ

## 5.4.2. አጠቃላይ መግለጫ

ማህበራዊ ሚዲያን አግባብ ባልሆነ መንገድ ከተጠቀምን የግል እና ማህበራዊ ገመናዎችን ሊጎዳ ይችላል። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አንዳንድ ማህበራዊ ሚዲያዎች ልጆችን ለጉዳት እያጋለጡ ይገኛሉ። ይህንንም ለመከላከል ሳያውቁ እራሳቸውን ለማህበራዊ ሚዲያ ጉዳት የሚያጋልጡትን በማረም ላይ ማተኮሩ ወሳኝ ነው። ይህን ካላደረግን እነዚህ ልጆች እንደ ተስፋ መቁረጥ፣ ጭንቀት እና ድብርት ባሉ አሉታዊ ሁኔታዎች ውስጥ ለመግባት ይገደዳሉ። እራሳቸውንና ማህበረሰቡን ሊጎዱ በሚችሉ ተግባራትም ተሳታፊ የመሆን እድላቸው ይጨምራል፡፡ ስለሆነም እኛ ችግሮቹ እንዳይከሰቱ አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባናል፤ ተከስተው ከተገኙም መፍትሔዎችን ማፈላለግና መተግበር ይጠበቅብናል።

## 5.4.3. የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ተንሸራታች ሥዕሎች፣ ምስሎች፣ በራሪ ጽሑፎች፣ ፊልሞች፣ ብሮሸሮች፣ ግራፎች፣ ካርታዎች፣ ሥዕሎች፣ ካርቶኖች

ምስል 1 የሚዲያ ስነምግባርን የማያከብሩ እና የሀገርን ስም የሚያጎድፉ የሀሰት መረጃዎችን የሚያሳይ ሲሆን ምስል 2 ደግሞ ሀይለኛው ደካማው ላይ ሲሳለቅበት ያሳያል።

## የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ትምህርቱ ከማቅረቡ በፊት በቂ ዝግጅት ማድረግ
- ማህበራዊ ሚዲያን በምንጠቀምበት ጊዜ ስለሚከሰቱ ስነምግባር የጎደላቸው ትግባራት ተማሪዎችን ጥያቄዎችን በመጠየቅ መጀመር
- የማህበራዊ ሚዲያ አላግባብ መጠቀም የሚያስከትለውን ጉዳት በተለያዩ ካርዶች ላይ በመጻፍ እና ተማሪዎች ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ጉዳቶች እንዲዘረዝሩ ማድረግ
- ትናንሽ ቡድኖችን በመፍጠር ተማሪዎች እንዲወያዩ እና የውይይት ሀሳባቸውን ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ማድረግ
- አሳታፊ ገለጻን መጠቀም፣ ማስታወሻ መስጠት
- የጥንድ፣ የቡድን እና የጋራ ውይይቶችን ማመቻቸት

## የትምህርቱ አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

የዕለቱን ትምህርት ከመጀመር በፊት ስላለፈው ትምህርት በማስታወስ ተማሪዎችን በማህበራዊ ሚዲያ ሲጠቀሙ የሚፈፀሙ ኢ-ሞራላዊ ድርጊቶች ምን ምን እንደሆኑ መጠየቅ።

### ለ. ይዘት

- የማህበራዊ ሚዲያ ያልተገባ አጠቃቀምን በተመለከተ በዝርዝር ማስረዳት
- ስነምግባር የጎደላቸው የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀሞች የሚያስከትሉት ጉዳት

### ሐ. ማጠናከሪያ

- ተማሪዎች በዕለቱ የተማሩትን ትምህርት እንዲያብራሩ ማትጋት፤
- የትምህርቱን ዋና ዋና ነጥቦች መልሶ በማንሳት ማጠናከር

### 5.4.4. ምዘና እና ክትትል

**ሀ. ምዘና**

- ትምህርቱን ለማጠናከር ሁል ጊዜ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ምዘና ማካሄድ።
- ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲረዱት ወዲያውኑ የክፍል ስራ መስጠት፣ በቡድን በማደራጀት ማህበራዊ ሚዲያን ስንጠቀም ስለሚፈጸሙ ኢስነምግባራዊ ተግባራት ምሳሌዎችን እያነሱ እንዲወያዩ በማድረግ መገምገም።
- የክፍል ውጪ ተግባራትን ማሰራት

**ለ. ክትትል**

- ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን ማረጋገጥ
- መልመጃዎችና ተግባራት መሰራታቸውን ማረጋገጥ

### 5.4.5. የትምህርት አራት ተግባራት መልስ

**ተግባር 4**

1. ማህበራዊ ሚዲያን ከመጠን በላይ መጠቀም ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት

ሀ. በማህበራዊ ሚዲያ ሱስ መያዝ

ለ. መሰደብ

ሐ. በማላገጥ ምክንያት ተጎጂ መሆን

መ. የሀሰት ዜና ማሰራጨት

ሠ. የግል እና የቡድን ምስጢሮች መሰራጨት

**2. ማህበራዊ ሚዲያ በመጠቀም ወቅት የተከለከሉ ነገሮች**

- ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር እና የይለፍ ቃልን ለሌሎች መስጠት
- ለማናውቃቸው ሰዎች ፎቶዎቻችንን ማጋራት
- የማናውቋቸውን ሰዎች ኢሜይሎች እና ሰነዶችን መክፈት
- ከማናውቀው ሰው ጋር በበይነ መረብ ሀሳብ መለዋወጥ

➢ የነውር ቃላትን መጠቀም

**ተግባር 5**

1. ከማህበራዊ ድህረ ገጽ ከእውነት የራቁ ዜናዎችን እንዲያመጣላቸው
2. አብዲን ትምህርቱን በአግባቡ በመከተል ስነ-ምግባርን እና ስነ-ምግባርን ጠበቀ

## የምዕራፍ ተግባራት መልሶች

**ትዕዛዝ 1፡ እውነት/ሀሰት**

1. ሀሰት 2. እውነት 3. ሀሰት 4. እውነት 5. ሀሰት

**ትዕዛዝ 2፡ አጭር መልስ**

1. ማህበራዊ ሚድያ የሚባሉት፡-

ሀ) ፌስቡክ ለ) ቴሌግራም ሐ) ዩቲዩብ

መ) እንስታግራም ሠ) ትዊተር እና ሌሎችም

2. ማህበራዊ ሚዲያ በስነምግባር ከተጠቀምንበት የሚከተሉት ጥቅሞች አሉት

ሀ) ከብዙ ሰዎች ጋር በአንድ ጊዜ መገናኘት እና መረጃን ማጋራት።

ለ) ከሌሎች ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት

ሐ) በየትኛውም የዓለም ክፍል ስለተከሰተ ክስተት ወዲያውኑ እንድናውቅ ያደርገናል።

መ) በሰፊው የማሰብ ችሎታን ማዳበር ወዘተ

# ምዕራፍ 6

# የባህል ግንኙነት

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ስለ ባህላዊ ግንኙነቶች፣ የባህል ግንኙነቶችን ትርጉም፣ የባህል ግንኙነቶችን አስፈላጊነት እና የባህላዊ ግንኙነቶች አመላካቾች ላይ ያተኮረ ይዘት ይቀርባል። የቡድን ውይይት፣ መረጃ መስጠት፣ ሠርቶ ማሳየት፣ ተግባራዊ እንቅስቃሴ፣ ጉብኝቶች፣ ጥያቄዎች እና የጽብረቃ ጽሑፎች የዚህ ምዕራፍ ትምህርቶችን ለማስተማሪያነት ጥቅም ላይ ይውላሉ። በእያንዳንዱ ትምህርት ተማሪዎችን ለማበረታታት ጥያቄዎች እና ተግባራት ይቀርባሉ፡ ማጠቃለያ እና የማጠቃለያ ጥያቄዎችም ተካተዋል። ቁልፍ ፅንሰ-ሀሳቦች ላይም ማብራሪያ ይሰጣል።

**የዚህ ምዕራፍ የመማር ውጤቶች፡-**

**በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ተማሪዎች፡-**

- የባህል ግንኙነቶችን ትርጉም ያብራራሉ፤
- ለባህላዊ ግንኙነቶች አስፈላጊነት ትኩረት ይሰጣሉ፤
- የባህል ግንኙነት ማሳያዎችን ይለያሉ፤
- ውጤታማ የባህል ግንኙነት መገለጫዎችን ያሳያሉ።

ለዚህ ምዕራፍ የተመደበው ጠቅላላ ጊዜ 18

**ትምህርቶች፡-**

ትምህርት 1፡ የባህል ግንኙነቶች ፍቺ

ትምህርት 2፡ የባህል ግንኙነት አስፈላጊነት

ትምህርት 3፡ በባህልና በሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) መካከል ያለው ግንኙነት

ትምህርት 4፡ የባህል ግንኙነቶች መገለጫዎች

# 6.1. ትምህርት 1፡ የባህል ግንኙነቶች ምንነት

**የክፍለ ጊዜ መጠን 3**

## 6.1.1. ይዘት

- የባህል ግንኙነቶች ምንነት

## 6.1.2. አጠቃላይ መግለጫ

ግላዊ እና ማህበራዊ መስተጋብርን መጀመርና ማዝለቅ በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ ወሳኝ ጉዳይ ነው። በባህሎች መካከል ያለ ግንኙነትን ማጥናት የማህበራዊ ሳይንስ መስክ መደበኛ ስራ ነው። ይህም የተለያዩ ባህልና ታሪክ ያላቸው ሰዎችን አብሮ የመኖር ባህላዊ ግንኙነት የሚመለከት ነው። የሰዎች የእርስበርስ መስተጋብር፣ ግለሰቦች ከሌሎች ሰዎች ጋር ከማህበራዊ ፍላጎታቸው አንጻር የሚኖራቸውን የግንኙነት አቅጣጫ የሚያመለክት ነው። ግለሰቦች ከሌሎች ጋር የሚገናኙባቸው ማህበራዊ ቡድኖች መካከል ዋና ዋናዎቹ ቤተሰብ፣ ጓደኝነት፣ መረዳጃ ማህበራት እና የተለያዩ ድርጅቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በነዚህም ውስጥ ተሳትፎ በማድረግ እራሳቸውን ይገነዘቡበታል።

## 6.1.3. የመማር ማስተማር ሂደት

### የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ፊሊፕ ቻርቶች፣ ፎቶግራፎች፣ ቪዲዮዎች፣ ፊልሞች፣ መጽሔቶች፣ ብሮሸሮች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ግራፊክስ፣ ፖስተሮች፣ ፎቶግራፎች፣ ካርታዎች፣ ካርቱኖች፣ መጽሔቶች እና ጋዜጦች።

የባህላዊ ግንኙነቶችን አስፈላጊነት በሚያሳይ ቻርት በባህሎች መካከል ውጤታማ የግንኙነት ስልቶች ላይ ማተኮር ይመረጣል፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

ውይይት፣ ክርክር፣ ሚና መጫወት፣ ተረት፣ ድራማ፣ ጥያቄ እና መልስ

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

የባህል ግንኙነቶችን ትርጉም በተሻለ ሁኔታ የሚያብራሩ ሥዕሎች፣ የትምህርት ዕቅዶች እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

ውድ መምህር! የቀደመውን ትምህርት በአጭሩ ይከልሱ እና የዕለቱን ትምህርት ርዕስ እንደ መግቢያ ያስተዋውቁ። ከተማሪዎቹ የቀደመ እውቀት ጋር በማዛመድም ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታቱ። ይህም የተማሪዎችን ትኩረት በመሳብ ለትምህርቱ ይዘት ማዘጋጀትን ይጨምራል።

**ለ. አቀራረብ**

ይህ ክፍል የእለቱን የመማር አላማ መንገር፣ ተማሪዎች ከአዳዲስ መረጃዎች ጋር ማስተዋወቅ እንዲሁም የትምህርቱን ትክክለኛ አጀማመር እና የመምህሩን እና የተማሪዎችን ተሳትፎን ያካትታል። ትምህርቶችዎ ውጤታማ እንዲሆኑ፣ የተለያዩ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን መጠቀም፣ መረዳትን የሚገመግሙ ጥያቄዎችን መጠቀም እና በተቻለ መጠን ከተማሪዎ ዘንድ ብዙ አስተያየቶችን ማግኘት አለብዎት።

**ሐ. ማጠናከሪያ**

መምህር፤ ተማሪዎችዎ እንዲሳተፉ ማድረግ ዋና ተግባርዎ እንደሆነ ይገንዘቡ፤ ተማሪዎችዎን ማረም ያለብዎት ሀሳባቸው ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ ለተማሪዎችዎ ስለቀረቡት ይዘቶች ወይም ጥያቄዎች አጭር አስተያየት ስጧቸው እና ከተሳሳቱ ያስተካክሉዋቸው።

**6.1.4. ምዘና እና ክትትል**

**ሀ) ምዘና**

ተማሪዎችን የተለያዩ ጥያቄዎች መጠየቅ።ለምሳሌ፡-

1. የባህል ግንኙነት ማለት ምን ማለት ነው?
2. የሰዎች መግባቢያ መንገዶች ምን ምን ናቸው?

3. በባህሎች መካከል አወንታዊ መስተጋብር መፍጠር ምን ጠቀሜታ አለው?

ለ) **ክትትል**

ተማሪዎች አዳዲስ ፅንሰ-ሀሳቦችን እና ክህሎቶችን ሲተገበሩ በመመልከት እውቀትና ክህሎቶቻቸውን መመዘን፣ ተማሪዎች አስተሳሰባቸውን እና አሰራራቸውን ምክንያታዊ እንዲያደርጉ ማስረጃዎችን በማደራጀት ማገዝ፣ ተማሪዎች እርስበርስ እየተገማገሙ የምዘናው አካል እንዲሆኑ ማበረታታት፣ ማመሳከሪያዎችን (ቼክ ሊስት) በመጠቀም የየዕለት ለውጦቻቸውን መመዝገብ፣ ገንቢ ምጋቤ ምላሾችን መስጠት የተወሰኑ የክትትል ስልቶች ናቸው ።

### 6.1.5. ትምህርት 1 ተግባራት መልስ

**ተግባር 1**

1. የባህል ግንኙነት ማለት ብሔሮች፣ ሔረሰቦችና ሕዝቦች በተለያዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አውዶች መስተጋብር መፍጠር ማለት ነው።

2. በስእል 6.1 ውስጥ ካሉት ልዩነቶች

ሀ) የሃይማኖት ልዩነቶች

ለ) የባህላዊ አልባሳት ልዩነቶች

ሐ) የቀለም (የፊት ገጽታ) ልዩነቶች

## 6.2. ትምህርት 2፡ የባህል ግንኙነት አስፈላጊነት

የክፍለ ጊዜ 5

### 6.2.1. ይዘት

ሀ. አዲስ ባህል መማር

ለ. አዳዲስ ክህሎቶችን መማር

ሐ. የተሳሳቱ አመለካከቶችን ማስወገድ

## 6.2.2 አጭር መግለጫ

በተለያዩ ባህሎች መካከል ያለ ግንኙነት የተለያዩ ተግዳሮቶች ሊያጋጥሙት ይችላል። ቢሆንም በባህሎች መካከል ያለ ግንኙነት እየጠነከረ በመጣ ቁጥር በርካታ ጠቀሜታዎች ሊያስገኝ ይችላል።

## 6.3.3. የመማር እና የማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ፊሊፕቻርቶች፣ ፎቶግራፎች፣ ቪዲዮዎች፣ ፊልሞች፣ ብሮሸሮች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ግራፊክስ፣ ፖስተሮች፣ ፎቶግራፎች፣ ካርታዎች፣ ካርቱኖች፣ መጽሔቶች፣ የባህላዊ ግንኙነቶችን አስፈላጊነት የሚያሳይ ቻርት እና ጋዜጦች

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

ውይይት፣ ክርክር፣ ሚና መጫወት፣ ተረት፣ ድራማ፣ ጥያቄ እና መልስ

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

በኢትዮጵያ እና በሌሎች ቦታዎች ያለውን የባህል ግንኙነት አስፈላጊነት የሚያብራሩ የመማሪያ ዕቅዶችን እና የመማሪያ መርጃዎችን ማዘጋጀት።

**የትምህርቱ አቀራረብ**

**ሀ. መግቢያ**

መምህር፤ ለተማሪዎችዎ የቀደመውን ትምህርት በአጭሩ ይከልሱ እና የእለቱን ትምህርት ርዕስ ያስተዋውቁ። የተማሪዎችን ፍላጎት ከቀደመ እውቀት ጋር በማዛመድ ያበረታቷቸው። ይህም የተማሪዎችዎን ተነሳሽነት በማነቃቃት ለእለቱ ትምህርት ማዘጋጀትን ይጨምራል።

**ለ. አቀራረብ**

ይህ ክፍል የእለቱን የመማር አላማ መንገር፣ ተማሪዎች ከአዳዲስ መረጃዎች ጋር ማስተዋወቅ እንዲሁም የትምህርቱን ትክክለኛ አጀማመር እና የመምህሩን እና የተማሪዎችን ተሳትፎን ያካትታል። ትምህርቶችዎ ውጤታማ እንዲሆኑ፣ የተለያዩ የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን መጠቀም፣ መረዳትን የሚገመግሙ

ጥያቄዎችን መጠቀም እና በተቻለ መጠን ከተማሪዎ ዘንድ ብዙ አስተያየቶችን ማግኘት አለብዎት።

**ሐ. ማጠናከሪያ**

መምህር፤ ተማሪዎችዎ እንዲሳተፉ ማድረግ ዋና ተግባርዎ እንደሆነ ይገንዘቡ፤ ተማሪዎችዎን ማረም ያለብዎት ሀሳባቸው ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ ለተማሪዎችዎ ስለቀረቡት ይዘቶች ወይም ጥያቄዎች አጭር አስተያየት ስጧቸው እና ከተሳሳቱ ያስተካክሉዋቸው።

### 6.2.4. ምዘና እና ክትትል

**ሀ. ምዘና**

የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ። ለምሳሌ የባህላዊ ግንኙነት ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?

**ለ. ክትትል**

አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦችን እና ክህሎቶችን ሲተገበሩ ተማሪዎችን ይከታተሉ፣ የተማሪዎችን እውቀት እና ችሎታ ይመዝኑ፣ ተማሪዎች አስተሳሰባቸውን ወይም ባህሪያቸውን መለወጣቸውን የሚያሳይ ማስረጃ በማደራጀት የተማሪዎችን የመማር ችሎታቸውን እና የቡድን ስራቸውን ይከታተሉ።

### 6.2.5. የትምህርት 2 ተግባራት መልስ

**ተግባር 2**

የባህል ግንኙነት ጥቅሞች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡፡

ሀ. አዲስ ባህል መማር

ለ. አዳዲስ ክህሎቶችን መማር

ሐ. የተሳሳቱ አመለካከቶችን ማስወገድ

መ. አብሮነትን ማጠናከር

# 6.3. ትምህርት 3፡ በባህልና በሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) መካከል ያለ ግንኙነት

የክፍለ ጊዜ መጠን 5

## 6.3.1 ይዘት

- የባህል እና የግሎባላይዜሽን ግንኙነት

## 6.3.2. አጠቃላይ መግለጫ

የባህል ግንኙነት መገለጫዎች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል የተወሰኑት ውጤታማ ግንኙነት፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት፣ ቀልጣፋ ግንኙነት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 6.3.3. የመማር ማስተማር ሂደት

### የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

ፊሊፕቻርቶች፣ ፎቶግራፎች፣ ቪዲዮዎች፣ ፊልሞች፣ ብሮሹሮች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ግራፊክስ፣ ፖስተሮች፣ ፎቶግራፎች፣ ካርታዎች፣ ካርቱኖች፣ መጽሔቶች እና ጋዜጦች።

የባህላዊ ግንኙነቶችን አስፈላጊነት የሚያሳይ ቻርት እና በባህሎች መካከል ውጤታማ የግንኙነት ስልቶች ላይ ማተኮር ይመረጣል፡፡

### የመማር ማስተማሪያ ዘዴዎች

ውይይት፣ ክርክር፣ ሚና መጫወት፣ ተረት፣ ድራማ፣ ጥያቄና መልስ

### የትምህርት ለቅድመ ዝግጅት

የሉላዊነት (የግሎባላይዜሽን) ትርጉም በተሻለ ሁኔታ የሚያብራሩ ፖስተሮች እንዲሁም  የትምህርት ዕቅዶችን እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ።

### ሀ. መግቢያ

የቀደመውን ትምህርት በአጭሩ ይከልሱ፤ የእለቱን ትምህርት ያስተዋውቁ። የተማሪውን የቀድመ እውቀት ከእለቱ ትምህርት ጋር በማዛመድ ያበረታቱ። ይህም ተማሪዎችን በማነሳሳት  ለትምህርቱ ያዘጋጃል።

### ለ. አቀራረብ

መምህር፤ ተማሪዎችዎ እንዲሳተፉ ማድረግ ዋና ተግባርዎ እንደሆነ ይገንዘቡ፤ ተማሪዎችዎን ማረም ያለብዎት ሀሳባቸው ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ ለተማሪዎችዎ ስለቀረቡት ይዘቶች ወይም ጥያቄዎች አጭር አስተያየት ስጧቸው እና ከተሳሳቱ ያስተካክሉዋቸው።

### ሐ. ማጠናከሪያ

መምህር፤ ተማሪዎችዎ እንዲሳተፉ ማድረግ ዋና ተግባርዎ እንደሆነ ይገንዘቡ፤ ተማሪዎችዎን ማረም ያለብዎት ሀሳባቸው ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ ለተማሪዎችዎ ስለቀረቡት ይዘቶች ወይም ጥያቄዎች አጭር አስተያየት ስጧቸው እና ከተሳሳቱ ያስተካክሉዋቸው።

## 6.2.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችዎን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ። ለምሳሌ ሉላዊነት/ ግሎባላይዜሽን በምን ይገለጻል?

### ለ. ክትትል

አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦችን እና ክህሎቶችን ሲተገበሩ ተማሪዎችን ይከታተሉ፣ የተማሪዎችን እውቀት እና ችሎታ ይመዝኑ፣ ተማሪዎች አስተሳሰባቸውን ወይም ባህሪያቸውን መለወጣቸውን የሚያሳይ ማስረጃ በማደራጀት የተማሪዎችን የመማር ችሎታቸውን እና የቡድን ስራቸውን ይከታተሉ።

## 6.3.5 የትምህርት 3 ተግባር መልስ

### ተግባር 3

1. ማህበራዊ አንድነትን ያዳክማል፣ እርስ በርስ ለመማማር እድሎችን እንቅፋት ይፈጥራል ወዘተ።

2. አዎ፡ የተለያዩ ብሔሮች ተመሳሳይ ባህሎችን ማዳበር ይችላሉ።

3.ሉላዊነት/ ግሎባላይዜሽን ያስከትላል

# 6.4. ትምህርት 4፡ የባህል ግንኙነቶች መገለጫዎች

**የክፍለ ጊዜ መጠን 5**

## 6.4.1 ይዘቶች

- ውጤታማ ግንኙነት
- ባህላዊ ግጭቶችን መፍታት
- ቀልጣፋ ግንኙነት

## 6.4.2. አጠቃላይ መግለጫ

የባህል ግንኙነቶች ብዙ መገለጫዎች አሏቸው። ጥቂቶቹ ውጤታማ ግንኙነት፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት፣ ቀልጣፋ ግንኙነት እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 6.4.3. የመማር ማስተማር ሂደት

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

ፊሊፕቻርቶች፣ ፎቶግራፎች፣ ቪዲዮዎች፣ ፊልሞች፣ መጽሔቶች፣ ብሮሹሮች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ ግራፊክስ፣ ፖስተሮች፣ ፎቶግራፎች፣ ካርታዎች፣ ~~ሥዕላዊ መግለጫዎች~~፣ ካርቱኖች፣ መጽሔቶች እና ጋዜጦች።

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

ውይይት፣ ክርክር፣ ሚና መጫወት፣ ተረት፣ ድራማ፣ ጥያቄዎች እና መልሶች

መምህር፤ የባህል ግንኙነቶችን በተመለከተ ድራማ በማዘጋጀት ለተማሪዎች አሳዩ። ካዩ በኋላ በጉዳዩ ላይ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ ጥቂት ተማሪዎችን ይጋብዙ።

**ቅድመ ትምህርት ዝግጅት**

የባህላዊ ግንኙነቶች መገለጫዎች በትክክል የሚገልጹ ሥዕሎችን፣ የትምህርት ዕቅዶችን እና የማስተማሪያ ቁሳቁሶችን ያዘጋጁ።

## የትምህርቱ አቀራረብ

### ሀ. መግቢያ

የቀደመውን ትምህርት በአጭሩ ይከልሱ፤ የእለቱን ትምህርት ያስተዋውቁ። የተማሪውን የቀድመ እውቀት ከእለቱ ትምህርት ጋር በማዛመድ ያበረታቱ። ይህም ተማሪዎችን በማነሳሳት  ለትምህርቱ ያዘጋጃል።

### ለ. አቀራረብ

መምህር፤ ተማሪዎችዎ እንዲሳተፉ ማድረግ ዋና ተግባርዎ እንደሆነ ይገንዘቡ፤ ተማሪዎችዎን ማረም ያለብዎት ሀሳባቸው ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ ለተማሪዎችዎ ስለቀረቡት ይዘቶች ወይም ጥያቄዎች አጭር አስተያየት ስጧቸው እና ከተሳሳቱ ያስተካክሉዋቸው።

### ሐ. ማጠናከሪያ

መምህር፤ ተማሪዎችዎ እንዲሳተፉ ማድረግ ዋና ተግባርዎ እንደሆነ ይገንዘቡ፤ ተማሪዎችዎን ማረም ያለብዎት ሀሳባቸው ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ ከሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ ለተማሪዎችዎ ስለቀረቡት ይዘቶች ወይም ጥያቄዎች አጭር አስተያየት ስጧቸው እና ከተሳሳቱ ያስተካክሉዋቸው።

## 6.4.4. ምዘና እና ክትትል

### ሀ. ምዘና

የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተማሪዎችዎን ግንዛቤ መገምገም ይችላሉ። ለምሳሌ ሉላዊነት/ ግሎባላይዜሽን በምን ይገለጻል?

### ለ. ክትትል

አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦችን እና ክህሎቶችን ሲተገበሩ ተማሪዎችን ይከታተሉ፣ የተማሪዎችን እውቀት እና ችሎታ ይመዝኑ፣ ተማሪዎች አስተሳሰባቸውን ወይም ባህሪያቸውን መለወጣቸውን የሚያሳይ ማስረጃ በማደራጀት የተማሪዎችን የመማር ችሎታቸውን እና የቡድን ስራቸውን ይከታተሉ።

### 6.4.5 የትምህርት 4 ተግባራት መልስ።

**ተግባር 4**

በክፍል ውስጥ ተማሪዎችዎን በተርታ ያስቀምጧቸው፡፡ ከዚያም መጀመሪያ ላይ ለተቀመጠው ተማሪ አንድ ቃል በዝግታ ድምፅ ይንገሩ፡፡ የመጨረሻው ረድፍ እስኪደርስ ድረስ እርስ በርሳቸው በለሆሳስ እንዲያስተላልፉ ያድርጉ። በመቀጠል መጀመሪያ የተቀመጠው ተማሪ ለቀጣዩ ተማሪ የነገረውን ቃል ጠይቁት በመጨረሻም የመጨረሻው ተማሪ የተናገረው ቃል ጋር አንድ አይነት መሆኑን ያረጋግጡ።

የመጨረሻው ተማሪ የተናገረው ቃል ከመጀመሪያው ተማሪ ጋር ተመሳይ ነው? የተለየ ከሆነ ለምን?

**ተግባር 5**

በባህል ውስጥ ያሉ ጉዳዮችን እንዲዘረዝሩ ያድርጉ

ለምሳሌ፣ ባህላዊ አልባሳት፣ ባህላዊ ምግቦች፣ ክብረ በዓላት፣ ታዋቂ ጥበብ፣ የደስታና የሀዘን መግለጫ መንገዶች፣ ወዘተ

## 6.5. የምዕራፍ 6 የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

**ትእዛዝ I: ውሸት ወይም እውነት**

1. እውነት 2. እውነት 3. እውነት 4. እውነት

**ትዕዛዝ II፡ ምርጫ**

1. ሐ 2.መ 3. ሐ 4.መ

**ትዕዛዝ III: ባዶ ቦታዎችን ይሙሉ**

1. የባህል ግንኙነት ጥናት

**ትዕዛዝ IV፡ በአጭሩ መልስ**

1. የባህል እርቅ ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች ጥቂቶቹ፡-

   ሀ) በባህላዊ መካከል ያሉ እንቅፋቶችን ማስወገድ

   ለ) የግጭት አፈታት

   ሐ) በኅብረተሰቡ ውስጥ ግልጽነትን እና ማካተትን ማሳደግ

2. የባህል ግንኙነቶች ጠቋሚዎች

   ሀ) ውጤታማ ግንኙነት

   ለ) ባህልን መገንዘብ

   ሐ) ንቁ ግንኙነት

# የ5ኛ ክፍል ግብረገብ ትምህርት መርሃ ትምህርት

## መግቢያ

ይህ መርሃ ትምህርት ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት የሚጠበቁ የመማር ውጤቶችን፣ ይዘትን፣ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን እና የምዘና ስልቶችን የሚገልጽ የ5ኛ ክፍል የግብረገብ ትምህርት መርሃ ትምህርት ነው። ይህ እንደአንድ የትምህርት አይነት የተዘጋጀው የግብረገብ ትምህርት ከግብረገብነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የያዘና ከተዘጋጁት ሌሎች መርሃ ትምህርቶች ጋርም ትስስር ያለው ነው። ለግብረገባዊነት ባህሪ መጎልበት መደበኛ ትምህርት ብቻ ሳይሆን፣ የቤተሰብ፣ የማህበረሰብና የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሁኔታዎች እንዲሁም የመምህራንና ሌሎች አካላት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

የግብረገብነት ትምህርት የ21ኛ ክፍለዘመንን ክህሎቶችና ከተማሪዎች የሚጠበቁ የመማር ውጤቶችን ማዕከል ያደረገ ነው። ዋነኛ ትኩረቱም ተማሪዎች መሰረታዊ ዕሴቶችን፣ ማህበራዊ ክህሎትን፣ በጥልቀት ማሰብን፣ የህይወት ዘመን ክህሎትን፣ ብዝሃ ባህልን፣ ማህበረሰብንና አለምን የመረዳት አቅም ባለቤት እንዲሆኑ ማገዝ ነው።

የግብረገብ ትምህርት እንደ መልካም ባህሪና ስነምግባር፣ ግለሰብና ማህበረሰብ፣ የባህልና ማህበረሰብ ጥናት የመሳሰሉ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ ነው። የዚህ ትምህርት ይዘትም ሞራልና ግብረገብነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው።

የግብረገብ ትምህርት መርሃ ትምህርት ግብ ተማሪዎች ባህልንና አጠቃላይ እሴቶችን አስመልክቶ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማስቻል ነው። በዚህም ተማሪዎች ከተለያየ ማህበራዊ ቡድንና ልዩ ልዩ ባህል ከመጡ ሰዎች ጋር ተከባብረው መኖርና መስራት እንዲችሉ ያስችላቸዋል።

ለ5ኛ ክፍል የግብረገብ ትምህርት የተዘጋጁ የመማር ውጤቶች፣ ይዘቶች፣ ብቃቶች፣ የመማር ማስተማር ብልሃቶችና የምዘና ስልቶች በሚከተለው ሰንጠረዥ ተዘርዝረው ቀርበዋል።

## ምዕራፍ አንድ፡- ኃላፊነትን መወጣት

**(የተመደበለት ክፍለጊዜ፡ 19)**

### የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፡-

- የኃላፊነት ምንነትን መረዳት
- ኃላፊነት መወጣትን ምንነት መግለጽ
- የኃላፊነት መወጣት አስፈላጊነትን መገንዘብ
- ኃላፊነት የመወጣት ደረጃዎችን መለየት
- የማህበረሰብን ሥነምግባሮችና እሴቶች ማድነቅና ማክበር

| ብቃት | ይዘት | የመማር ማስተማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የኃላፊነት ጽንሰሃሳብን ይገልጻሉ<br>• የራስ ኃላፊነትን መወጣት | 1.1 የኃላፊነት ምንነት<br>1.2 ኃላፊነትን መወጣት<br>1.3 ኃላፊነትን | • የኃላፊነት ምንነትን በተመለከተ የጥንድ ውይይት<br>• ኃላፊነት የመወጣት አስፈላጊነትን በተመለከተ | ✓ ተማሪዎች ሲወያዩ በመዘዋወር ምልከታ ማድረግ<br>✓ ኃላፊነት የመወጣት አስፈላጊነትን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • ለኃላፊነት መውሰድ አስፈላጊነት ትልቅ ቦታ መስጠት | የመወጣት አስፈላጊነት<br>1.4 የኃላፊነት ደረጃዎች<br>1.5 ግብረገባዊነት | ተማሪዎችን በማሳተፍ በአነስተኛ ቡድን መወያየት<br>• የኃላፊነት ደረጃዎች ላይ መወያየት<br>• ተማሪዎች ግብረገብና ግብረገባዊነትን በተመለከተ ሐሳባቸውን እንዲያጋሩ ማትጋት | በተመለከተ እንዲናገሩ መጠየቅ<br>✓ የኃላፊነት አይነቶችን በተመለከተ የቃል ጥያቄ ማቅረ<br>✓ ምጋቤ ምላሽ መስጠት |

## ምዕራፍ ሁለት፡- ጠንክሮ የመስራት ባህል

**(የተመደበለት ክፍለጊዜ፡ 20)**

**የዚህ ምዕራፍ የመማር ውጤቶች፡-**

- ጠንክሮ የመስራት ባህልን ምንነት መግለጽ
- ጠንክሮ የመስራት ባህል አስፈላጊነትን መገንዘብ
- ጠንክሮ የመስራት ባህል ያለውን ሰው ባህሪያት መዘርዘር
- የግል ስራን ማቀድ የሚቻልባቸውን መንገዶች ማወቅ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ማስተማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የጠንክሮ መስራት ጽንሰሃሳብን መግለጽ<br>• ጠንክሮ የመስራት ባህልን ማድነቅ<br>• ጠንክሮ የመስራት | 2.1 ጠንክሮ የመስራት ባህል ምንነት<br>2.2 ጠንክሮ የመስራት ባህል አስፈላጊነት<br>2.3 የጠንካራ ተማሪዎች የስራ ባህል | • ጠንክሮ መስራን በተመለከተ የጥንድ ውይይት<br>• ጠንክሮ የመስራት ባህልን አስፈላጊነት የተመለከተ የቡድን መወያየት<br>• ጠንክሮ የመስራት ባህል | ✓ ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>✓ በውይይት ወቅት ምልከታ ማድረግ<br>✓ ገንቢ ሀሳብ መስጠት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መገለጫዎችን መለየት | ማሳያዎች<br>2.4 የማንበብ ባህል<br>2.5 የማንበብ ባህልን የሚያጎለብቱ ብልሃቶች | መገለጫዎችን የተመለከተ ውይይት<br>• ተማሪዎች ያላቸውን የማንበብ ባህል በተመለከተ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ<br>• ተማሪዎች ያሏቸውን የማንበብ ልምዶች ለሌሎች እንዲያጋሩ ማትጋት | ✓ ጠንክሮ የመስራት ባህልን በተመለከተ ጥያቄና መልስ ማካሄድ<br>✓ ምጋቤ ምላሽ መስጠት |

## ምዕራፍ ሦስት፡ ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ችሎታ

**(የክፍለጊዜ ብዛት፡ 20)**

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ የትምህርት ውጤቶች፡-

- ውሳኔ የመስጠት ጽንሰ ሃሳቦችን መረዳት
- ተገቢ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ችሎታዎች ባህሪያትን መዘርዘር
- ምክንያታዊ ለሆነ ውሳኔ ትልቅ ስፍራ መስጠት
- ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ቅደም ተከተሎች እንዴት ስራ ላይ እንደሚውሉ ማሳየት
- ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት እንቅፋት የሆኑ ነገሮችን ለይቶ ማወቅ

| ብቃት | ይዘት | የመማር ማስተማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ትክክለኛ ውሳኔን መበየን<br>• የትክክለኛ ውሳኔ ባህሪያትን ይለያሉ<br>• ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነትን ማስረዳት<br>• ትክክለኛ ውሳኔ አለመስጠት | 3.1 ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ጽንሰሀሳቦች<br>3.2 ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ባህሪያት<br>3.3 ትክክለኛ ውሰኔ ለመስጠት የሚታለፍባቸው | ቡድን መስርቶ ተማሪዎችን በየቡድኑ በመመደብ፡-<br>• ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አካሄድ ላይ መወያየት<br>• ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አካሄድ ላይ ክርክር ማድረግ | • ጥያቄዎችን መጠየቅ<br>• በውይይት ወቅት ምልከታ ማካሄድ<br>• ገንቢ ሃሳብ መስጠት<br>• ጠንክሮ የመስራ ባልን በተመለከተ ጥያቄና |

| | | | |
|---|---|---|---|
| የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች መግለጽ<br>● ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮችን ይለያሉ | ደረጃዎች<br>3.4 ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት አስፈላጊነት<br>3.5 ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት እንቅፋቶች | • ትክክለኛ ውሳኔ የመስጠት ደረጃዎች እና እንቅፋቶቹ ላይ መወያየት<br>• ሚና ጨዋታ፣ ስዕሎችንና የጉዳይ ጥናትን በመገልገል ትክክለኛ ውሳኔ መስጠትን መለማመድ | መልሶች<br>● መልሶቻውን በማየት ምጋቤ ምላሽ መስጠት |

# ምዕራፍ አራት፡ የአካባቢ እንክብካቤ

**(የተመደበ ክፍለጊዜ፡ 19)**

## የምዕራፍ ትምርቱ የመማር ውጤቶች፡-

- የአካባቢ እንክብካቤ ምንነትን ማወቅ
- አከባቢ በመንከባከብ የሚገኝ ውጤትን ማድነቅ
- አካባቢ እንክብካቤ የሚካሄድባቸውን መንገዶች መግለጽ
- አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች መዘርዘር

| ብቃት | ይዘት | የመማር ማስተማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የአካባቢ እንክብካቤ ጽንሰሀሳቦችን መግለጽ<br>• አካባቢን የመንከባከብ ፍቅርን ማሳየት<br>• አካባቢን የመንከባከቢያ መንገዶችን መለየት<br>• አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች | 4.1 የአካባቢ ምንነትን መረዳት<br>4.2 የአካባቢ ክብካቤ ምንነት<br>4.3 የአካባቢ እንክብካቤ አስፈላጊነት<br>4.4 አካባቢን የመንከባከቢያ መንገዶች<br>4.5 አካባቢን ባለመንከባከብ | • ተማሪዎች የአካባቢ እንክብካቤን ምንነትን እንዲናገሩ መጠየቅ<br>• አካባቢ እንክብካቤን በተመለከተ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• አካባቢን አለመንከባከብ የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች | • በውይይት ወቅት ምልከታ ማካሄድ<br>• ክርክርና ገለጻ<br>• የተማሪዎችን ስራዎች |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ማስረዳት | የሚያስከሰቱ ጉዳቶች | በተመለከተ ተማሪዎች ክብ ሰርተው እንዲወያዩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት | መልሶ መመዝገብ<br>• ጥያቄና መልሶች<br>• የሙከራ ፈተናና ገለጻ<br>• ትምህርቱን ለማጠናከር ምጋቤ ምላሽ መስጠት<br>• ሙከራና ፈተና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ መስጠት |

## ምዕራፍ አምስት፡ የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር

**(የተመደበለት ክፍለጊዜ፡ 19)**

### የምዕራፉ የመማር ውጤቶች፡-

- ማህበራዊ ሚዲያ ማለት ምን ማለት እንደሆነ መግለጽ
- የማህበራዊ ሚዲያ አይነቶችን መዘርዘር
- የማህበራዊ ሚዲያ አስፈላጊነትን ማስረዳት
- ማህበራዊ ሚዲያን የመጠቀም ስነምግባሮችን መለየት
- ማህበራዊ ሚዲያን አላግባብ በመጠቀም የተነሳ የሚከተሉ ጉዳቶችን መለየት

| ብቃት | ይዘት | የመማር ማስተማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • ማህበራዊ ሚዲያ ምን እንደሆነ መግለጽ<br>• ለማህበራዊ ሚዲያ አስፈላጊነት ዋጋ መስጠት | 5.1 የማህበራዊ ሚዲያ ምንነት<br>5.2 የማህበራዊ ሚዲያ አስፈላጊነት<br>5.3 ማህበራዊ ሚዲያዎችን | • ተማሪዎች ማህበራዊ ሚዲያን በተመለከተ በአነስተኛ ቡድኖች እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ጥንድ ጥንድ ሆነው ማህበራዊ ሚዲያ አይነቶች ላይ እንዲነጋገሩ ማድረግ<br>• አራት አራት አባላት ያላቸው ቡድኖች በመመስረት | • ተማሪዎች ማህበራዊ ሚዲያ ምን ማለት እንደሆነ እንዲናገሩ መጠየቅ<br>• የተማሪዎቹ ተግባር ከሚጠበቁ የመማር ውጤቶች ጋር አዛምዱ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባርን መተግበር<br>• ማህበራዊ ሚዲያን አለአግባብ መጠቀም የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች መዘርዘር | የመጠቀመሚያ ስነምግባር<br>5.4 ማህበራዊ ሚዲያን ያላግባብ መጠቀም የሚያስከትላቸው ጉዳቶች | የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ስነምግባር ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• ማህበራዊ ሚዲያን አላግባብ መጠቀም የሚያስከትላቸውን ጉዳቶ የሚያሳዩ ፎቶግራፎችና ቪዲዮዎችን መጠቀም | • ተማሪዎች በተማሯቸው ጉዳዮች ላይ ጥያቄና መልስ<br>• የተማሪዎቹ ግንዛቤ ላይ በመመስረት ምጋቤ ምላሽ መስጠት |

# ምዕራፍ ስድስት፡ የባህል ትስስር

**(የተመደበለት ክፍለጊዜ፡ 15)**

## ከምዕራፍ ትምህርቱ የሚጠበቁ የመማር ውጤቶች፡-

- የባህል ትስስር ምንነትን መግለጽ
- የባህል ትስስር አስፈላጊነትን ማድነቅ
- የባህል ትስስርን የሚያጠናክሩ ጉዳዮችን መለየት
- ውጤታማ ለሆነ ተግባቦት ዋጋ መስጠት

| ብቃት | ይዘት | የመማር ማስተማር ብልሃቶች | ምዘና |
|---|---|---|---|
| • የባህል ትስስር ጽንሰሀሳቦችን መግለጽ<br>• የባህል ትስስር ማህበረሰብን ከመገንባት አንጻር ያለውን አስተዋጽዖ ማድነቅ<br>• የባህልና የሉላዊነትን(ግሎባላይዜሽን) ግንኙነት ማስረዳት | 6.1 የባህል ትስስር ምንነት<br>6.2 የባል ትስስር አስፈላጊነት<br>6.3 የባህልና ሉላዊነት ትስስር<br>6.4 የባህል ትስስር ማሳያዎች<br>• ውጤታማ ተግባቦት | • ተማሪዎች በባህሎች መካከል ያለው ትስስር ምን እንደሆነ በአነስተኛ ቡድኖች ሆነው እንዲወያዩ ማድረግ<br>• የፒራሚድ ስልትን በመጠቀም በባህላዊ ትስስር አስፈላጊነት ላይ እንዲወያዩ ማድረግ<br>• የባህል ትስስር ማሳያዎችን ለማስተማር የሚረዱ ምስሎችና | • የቡድን ውይይት ምልከታ<br>• የተማሪዎችን ክርክርና ስራ መልሶ መመዝገብ<br>• ጥያቄና መልስ<br>• ሙከራዎችና ገለጻ<br>• መማርን ለማጠናከር ምጋቤ ምላሽ መስጠት<br>• ሙከራና ፈተናን አስፈላጊ በሆነ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| • የባህል ትስስር ማሳያዎችን መናገር | • የውጤታማ ተግባቦት ማሳያዎች<br>• የባህል መናበብ<br>• የነቃ ተግባቦት ባለቤት መሆን | ቪዲዮዎች መጠቀም | ጊዜ መስጠት |